# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 235 ሚያዝያ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## «ቃል፤ ተግባር፤ ትውልድ»

## የመጻሕፍት አውደ ርዕይ ተከፈተ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- «ቃል፤ ተግባር፤ ትውልድ» በሚል መሪ ቃል በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አዘጋጅነት ለስድስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ የመጻሕፍት አውደ ርዕይ በአብርሆት ቤተ-መጻሕፍት ተከፈተ። በአውደ ርዕዩ ላይ በአብርሆት ቤተ-መጻሕፍት ቋሚ «የጠቅላይ ሚኒስትር ቤተ ንባብ» ይፋ ሆኗል።

«በጠቅላይ ሚኒስትር ቤተ ንባብ» ላይ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ አንስቶ ለንባብ ያበቋቸው መጻሕፍት ቀርበዋል። በአብርሆት የተዘጋጀው የመጻሕፍት አውደ ርዕይ ከሚያዝያ 24 እስከ ሚያዝያ

"ቃል፤ ተግባር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከታክስ ነፃ የሚገቡ ምርቶች ዋጋ ንረት አንድምታና የመፍትሄ አማራጮች

**ሞገስ ተስፋ**

መንግሥት በምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች ላይ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ለማርገብ የተለያዩ የመፍትሔ አማራጮችን እየወሰደ ነው። በተለይም ከውጭ የሚገቡ እንደ ፓስታ፤ ማካሮኒ፤ ዱቄትና የሕፃናት ምግቦች፣ የምግብ ዘይትና የመሳሰሉት ምርቶች ላይ የነበረውን ታክስ በማንሳት ከታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በፍራንኮ ቫሉታ በኩል መፍቀዱ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ የእነዚህ ምግቦች ዋጋ አሁን ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ ለኅብረተሰቡ ፈታኝ ሆነው እየተስተዋሉ ነው። ይህ ለምን ሆነ፤ እያጋጠመ ያለውን የዋጋ ንረት ለመግታት የመፍትሔ እርምጃዎች

ከታክስ ነፃ የሚገቡ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ዚያድ አባዲ



አቶ ኃይሉ ጀልዴ



አቶ ሀሩና አህመድ

## «በአዲስ አበባ የተገነቡ ፕሮጀክቶች በቀጥታ የሕዝብን ችግር ፈቺ ናቸው»

- የተለያዩ ከተማ ከንቲባዎች

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የተሠሩት ፕሮጀክቶች በቀጥታ ከሕዝብ ጋር የሚገናኙና ችግር ፈቺ መሆናቸውን የተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ከንቲባዎች ገለጹ።

የጂግጂጋ ከተማ ከንቲባ አቶ ዚያድ አብዲ፤ አዲስ አበባ ከተማ የተሠሩና በመሠራት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን

"በአዲስ አበባ የተገነቡ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## የሰንበት ገበያዎች የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት አወንታዊ ሚና እየተጫወቱ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የሰንበት ገበያዎች የግብይት ሰንሰለትን በማሳጠር ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በቀጥታ ለሸማቹ በማቅረብ በአገሪቱ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት ትልቅ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን የኢኮኖሚ ባለሙያው ገለጹ። ሸማቾች በበኩላቸው ከሌሎች የሸቀጥ መደብሮች ጋር ሲነጻጸር በሰንበት ገበያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶችን እያገኙ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማህበር ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር አረጋ ሹመቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰንበት የገበያ ሥርዓት ረጅሙን የገበያ ሰንሰለት በማሳጠር በቀጥታ ምርቶችን ከአምራቾች እና

የሰንበት ገበያዎች ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል




# ሴቶችን በፈጠራ ሥራዎች የበለጠ በማሳተፍ ውጤታማነታቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ሴቶችን በፈጠራ ሥራዎች የበለጠ እንዲሳተፉ በማገዝ ውጤታማነታቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል ሲል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

‹‹ሴቶችና አዕምሯዊ ንብረት፣ ኢኖቬሽንና ፈጠራን ለማፋጠን›› በሚል መሪ ሀሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ21ኛ፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ20ኛ ጊዜ የአዕምሯዊ ንብረት ቀን ተከብሯል፤

በወቅቱ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ወይዘሮ ኤርጎጌ ተስፋዬ እንደተናገሩት፤ በተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ መሥራት ያስፈልጋል።

አሁንም ሴቶች በአዕምሯዊ ንብረት፣ ኢኖቬሽንና ፈጠራን ዘርፉ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ያደረገ አይደለም ያሉት ሚኒስትሯ፤ የቴክኖሎጂን ዕድገት ለማፋጠን እና የፈጠራ ሥራዎችን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሴቶችን አቅም መጠቀም የግድ ይላል ሲሉ አስረድተዋል።

ሚኒስትሯ እንደገለጹት፤ የአዕምሯዊ ንብረት ቀን ሴቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መከበሩ ሴቶችን በቴክኖሎጂና ፈጠራ ለማሳተፍና ውጤታማ ለማድረግና በኢኮኖሚውም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ይረዳል።

የሴቶችን ተሳትፎ ካላሳደግን ወደምንፈልገው



**ወይዘሮ ኤርጎጌ ተስፋዬ**

የቴክኖሎጂ አቅም ለመድረስ እና ፈጠራዎችን ለማበራከት እንቸገራለን። በመሆኑም በፈጠራ ሥራዎች ሂደት የፆታ ተዋጽኦን እንዲለመድ በማድረግ እንደአገር ውጤት ማምጣት ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ሴቶችን በፈጠራና በሳይንስ ተጠቃሚ ለማድረግ በርካታ ፖሊሲዎችን ቀርጻ እየሠራች ትገኛለች ያሉት ሚኒስትሯ፤ በተለይም ሴቶችን በሴክተሩ ለማብቃት ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የሳይንስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የአሠራር መርሆችን በመቅረጽ ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት እየተንቀሳቀሰች መሆኑን ጠቁመዋል።

ሚኒስትሯ እንዳስታወቁት፤ ሴቶች የሠሯቸው የአዕምሯዊ ውጤቶች በሌሎች ሲነጠቁባቸውና በአግባቡ ዕውቅና ሳያገኙ የሚቀረቡበት ሁኔታ አለ። ስለሆነም ችግሮቹን ለመፍታት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የሚያከናውኗቸውን ጥረቶች ማጠናከር ይኖርባቸዋል።

በተጨማሪ ማህበረሰቡ ሴቶች ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን በተለይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ በሥራ ፈጣሪ ሴቶች ላይ የሚደርሱ ዛቻዎችና ጥቃቶች መከላከል አለበት ብለዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሁሪያ አሊ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በሴቶች ተጠቃሚነት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች በዋናነት የሚጎዱት ሴቶችን ቢሆንም የአገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወደኋላ የሚጎትቱ በመሆናቸው በትኩረት መሥራት ይገባል።

የማህበረሰቡን 50 በመቶ ሕዝብ አሳታፊ ሳያደርጉ ዕድገትን እና ብልጽግናን ማሳካት የማይታሰብ ነው ያሉት ወይዘሮ ሁሪያ፤ ሴቶችን በፈጠራ ሥራዎች የበለጠ በማሳተፍ ለአገር ያላቸውን አበርክቶ ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሴቶችን የሚያሳትፉ ፕሮጀክቶችን ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። የሴቶችን ተሳታፊነት ለማሳደግ ሁላችንም የራሳችንን ድርሻ መወጣት ዘመኑ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

# የፌስቲቫሉ መዘጋጀት የኢትዮጵያን የሰርከስ ዕድገትና አቅም ለማሳየት ይረዳል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚካሄደው አገር አቀፍ የሰርከስ ፌስቲቫል የስፖርቱን ዕድገትና አቅም ለዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት ለማሳየት እንደሚረዳ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኪነ ጥበብና ሥነጥበብ ፈጠራ ልማት ማስፋፊያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተፈሪ ተክሉ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን አገር አቀፍ የሰርከስ ፌስቲቫል ከሚያዝያ 27 እስከ 29 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ የኢትዮጵያ ባህል ማዕከል ይካሄዳል።

የሰርከስ ፌስቲቫሉ መካሄዱ ስፖርቱን እንደ ኪነጥበብ በመገንዘብ ኢትዮጵያ ያሏትን ጥበባዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶችን ለተቀረው ዓለም ለማስተዋወቅ ይረዳል ብለዋል።

የሰርከስ ስፖርት ከሌሎች ጥበባት ባልተናነሰ ሁኔታ ለመዝናኛነት ያገለግላል ያሉት አቶ ተፈሪ፤ ፌስቲቫሉ በስፖርቱ ዘርፍ የገበያ ትስስርን በመፍጠር ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካ የሰርከስ ዘርፍ ጠንካራ መሠረትን የሚጥልና የስፖርት ትርዒቶችን የዝግጅት አቅም የሚያሳድግ እንደሆነ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰርከስ ማህበር ጥምረት ፕሬዚዳንት ተክሉ አሻግር በበኩላቸው እንዳስታወቁት፤ ለሦስት ቀናት በሚቆየው የሰርከስ ፌስቲቫል ላይ ከ20 ሺህ በላይ ታዳሚዎች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ከሰባት ክልሎች የተውጣጡ 43 የሰርከስ ቡድኖች እና 250 የሰርከስ አርቲስቶች ትርዒቶቻቸውን እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል።

በዝግጅቱ ላይ ከ80 በላይ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የባህል እሴቶች በጥበብ መልክ ለዕይታ ይቀርባሉ። በሰርከስ ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎችና የስፖርቱ ባለሙያዎች በጋራ የሚሠሩበት በዓለም አቀፍ ዕድል እንደሚፈጠር ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።




ከፌስቲቫሉ በተጓዳኝነት በስፖርቱ ዘርፍ የሚካሄዱ ስብሰባዎችና የልምድ ልውውጥ መድረኮች ይከናወናሉ ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ዓለም አቀፍ የሰርከስ ድርጅቶች ስፖርቱን ለመደገፍና ተወዳዳሪዎችን ለመመልመል እንደሚመጡ አሳውቀዋል። ፌስቲቫሉ ለስፖርቱ ዕድገት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው።

የኢትዮጵያ ሰርከስ ፌስቲቫል ዓላማው ሁሉንም የሰርከስ ቡድኖች በማሰባሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ ስፖርቱን የበለጠ ለማስተዋወቅና በዓለም አቀፍ ደረጃ መልካም ተሞክሮዎች ለመለዋወጥ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተጨማሪ ፌስቲቫሉ የኢትዮጵያን የሰርከስ እድገትና አቅም ለአገርና ለዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት ለማሳየት እንዲሁም በኢትዮጵያ ሰርከስ ኩባንያዎችና ድርጅቶች መካከል ጠንካራና አወንታዊ ግንኙነት ለመፍጠር አላማ አድርጓል ብለዋል።

በፌስቲቫሉ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ተሳትፈው ሽልማቶችን ያገኙ ተወዳዳሪዎችና የሰርከስ ቡድኖች ሥራዎቻቸውን እንደሚያቀርቡ ተገልጿል።



አቶ ካሳሁን ገለታ

# ከቡና የውጭ ንግድ ከ896 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከቡና የውጭ ንግድ ከ896 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ። ከሻይ ቅጠል ምርት አንድ ነጥብ 83 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንደተገኘም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ገለታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለሥልጣኑ በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት 243 ሺ 659 ቶን ቡና በመላክ አንድ ነጥብ 19 ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 163 ሺ 666 ቶን የቡና ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ 896 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

በምርት መጠን የዕቅዱን 67 በመቶ፣ በገቢ ደግሞ የእቅዱን 75 በመቶ ማሳካት መቻሉን አመልክተው፤ የዕቅድ አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸርም በመጠን 22 ነጥብ 4 በመቶ ቅናሽ እንዲሁም በገቢ ሁለት ነጥብ 36 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ እንደሚያሳይ ተናግረዋል።

221 ሺ 883 ቶን የቡና ምርት በተለያዩ የግብይት አማራጮች ለአገር ውስጥ ገበያ ለሽያጭ የቀረበ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህም አንድ ሚሊዮን 062 ሺ 34 ሄክታር መሬት በቡና ተሸፍኖ እንደነበርና 5 ነጥብ 8 ሚሊዮን አርሶ አደሮች መሳተፋቸውን አስታውሰዋል።

የዓለም ገበያ መዋዠቅ፣ የቡና ዋጋ በተለይም ከጥቅምት ወር ጀምሮ ከ20 እስከ 25 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱ፣ የገዥዎች ፍላጎት መቀነስ፣ በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ የባቡር ትራንስፖርት በመቆሙ 4800 የሚሆን የቡና ምርት ለማጓጓዝ ችግር ማጋጠሙ እንደ ተግዳሮት የሚጠቀሱ ናቸው ብለዋል።

በተያያዘም ባለሥልጣኑ አንድ ሺህ 476 ነጥብ 79 ቶን ሻይ ቅጠል ምርት ለውጭ ገበያ በመላክ ሁለት ነጥብ 49 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 806 ነጥብ 61 ቶን የሻይ ቅጠል ምርት በመላክ አንድ ነጥብ 83 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል ብለዋል።

ይህም እቅዱን በመጠን 55 በመቶ ፤ በገቢ ደግሞ 74 በመቶ ማሳካት መቻሉን ገልጸው፤ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸርም በመጠን ሁለት ነጥብ 9 በመቶ ጭማሪ እና በገቢ ሁለት ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ ማሳየቱን አቶ ካሳሁን ገልጸዋል።

እስካሁን በአገሪቱ 3 ሺህ 377 ሄክታር መሬት በሻይ ቅጠል ምርት የሚሸፍን መሆኑን ገልጸው፤ ሽፋኑን ለማሳደግ የግል ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ ብለዋል።

በተለይ እንደ ችግር የሚነሱትን የኤሌክትሪክ ኃይልና የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ለመመለስ ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ባለሥልጣኑ የሻይ ልማት ስትራቴጂ በማዘጋጀት በትኩረት እየሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ባለሀብቶችም ወደ ዘርፉ በስፋት በመግባት አገራቸውንና ራሳቸውን እንዲጠቅሙ ጥሪ አቅርበዋል።

ዜና

# ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ በተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ የ9 ቀናት የምርመራ ጊዜ ተፈቀደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕገ መንግሥቱንና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ ሲንቀሳቀሱ ነበር ተብለው በተጠረጠሩ 11 ግለሰቦች ላይ ፍርድ ቤቱ የዘጠኝ ቀን የምርመራ ማጣሪያ ጊዜ ፈቀደ።

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት በ11 ተጠርጣሪዎች ላይ ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወንባቸው የዘጠኝ ቀን ተጨማሪ ጊዜ የፈቀደው ፖሊስ የሠራውን ምርመራ ሥራ ተመልክቶ ነው።

ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግባቸው የዘጠኝ ቀናት ጊዜ ቀጠሮ የተፈቀደባቸው ተጠርጣሪዎች ጌታሆይ አለሙ ተበጀ፣ ሀብታሙ ዳኜ ፣ ዳዊት አባቡ፣ ቴድሮስ ተሾመ፣ ጌታቸው ጥዑመ ልሳን፣ ትዛዙ ታረቀኝ፣ ሙሉቀን ወንዴ፣ ዋና ሳጅን ቢያዝን ምህረቱ፣ ምስጋና ማሩ፣ ዶክተር በቀለ ኃይሌ፣ ጌትነት ወንደሰን ናቸው።

መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹ ሕገ መንግሥቱንና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ በማሰብ በኢ - መደበኛ አደረጃጀት በመፍጠር በአማራ ክልል ሁከትና ብጥብጥ አመፅ በማስነሳት በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ወንጀል ተሳትፎ አላቸው በማለት የምርመራ ሥራ እያከናወነባቸው እንደሚገኝ ለችሎቱ ገልጿል።

በዚህም በጀመረው ምርመራ ሥራ ተጠርጣሪዎቹ ኢ - መደበኛ መዋቅራዊ አደረጃጀት ፈጥረው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር ማስረጃ ሰብስበናል ሲል ለችሎቱ አብራርቷል።

ለወንጀል ተሳትፏቸው የሚያስረዱ የምስክሮችን ቃል መቀበሉን እና በእጃቸው ላይ የተገኙ ኤሌትሮኒክስ መሣሪያዎችን ለሚመለከተው አካል እንዲመረመር መላኩን አስረድቷል።

የገንዘብ ዝውውርን በሚመለከት ለማጣራት ለባንኮች ማስረጃ መጠየቁንም ፖሊስ አብራርቷል። ተጨማሪ ምስክር ቃል ለመቀበል እና ቀሪ ሥራዎችን አከናውኖ ለማቅረብ የ14 ቀን ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ነበር።

ተጠርጣሪዎቹ ጠበቆች በበኩላቸው ለፖሊስ ከዚህ በፊት የተሰጠው ጊዜ በቂ መሆኑን ጠቅሰው ተጨማሪ የምርመራ ቀናት ሊሰጥ አይባም በማለት ተከራክረዋል። በተጨማሪም የተጠርጣሪዎቹ የዋስትና መብት እንዲፈቀድ ጠይቀዋል።

መርማሪ ፖሊስ በበኩሉ ተጠርጣሪዎቹ በዋስ ቢወጡ ምስክር ሊያስፈራሩና ሊደልሉብን እንዲሁም በመንግሥት የተጀመረውን የሕግ ማስከበር ሥራ ሊያደናቅፉ ይችላሉ ሲል ስጋቱን ገልጾ የዋስትና ጥያቄያቸውን ተቃውሟል።

የግራ ቀኙን ክርክር ያዳመጠው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ የፖሊስን የምርመራ መዝገቡን አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ የቴክኒክና የፎረንሲክ ማስረጃዎች መሰብሰባቸውን መመልከቱን አብራርቷል።

በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪዎቹ የጠየቁትን የዋስትና ጥያቄን ለጊዜው ውድቅ በማድረግ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው ሲል ለፖሊስ የ9 ቀን የምርመራ ጊዜ ፈቅዷል።

# የግል ከፍተኛ ተቋማትን እንደአዲስ በመመዝገቡ ሂደት መመዘኛውን የማያሟሉ ፈቃዳቸው ይነጠቃል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የግል ከፍተኛ ተቋማትን እንደአዲስ በመመዝገቡ ሂደት መመዘኛውን የማያሟሉ ፈቃዳቸው የሚነጠቅ መሆኑን የትምህርት ስልጠና ባለስልጣን አስታወቀ።



አቶ ቸሩ ጌታ ገነነ

የትምህርት ስልጠና ባለስልጣን የተቋማት ቁጥጥር ኢንስፔክሽንና የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ቸሩጌታ ገነነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሚፈለገው ደረጃ የትምህርት ጥራቱን ለማረጋገጥ እና የተሟላ የትምህርት ተቋማት መረጃ እንዲኖር የግል ከፍተኛ ተቋማትን እንደአዲስ መመዝገብ አስፈልጓል።

ከዚህ ቀደም የነበሩ መመዘኛዎች በትክክል የሚፈለገውን የትምህርት ጥራት ማምጣት የሚችሉ እንዳልነበሩ ያብራሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንደአዲስ ፈቃድ መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት ከዚህ ቀደም በነበረው ምዝገባ በተቋማቱ ሳይሟሉ የቀሩ ማስረጃዎች እንዳሉ ተናግረዋል። በዚህም ስለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያሉ መረጃዎች የጥራት ጉድለት እንዳለባቸው አብራርተዋል።

እንደ አቶ ቸሩጌታ ገለጻ፤ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ቁጥራቸው በ60 በመቶ ጨምሯል። የታየው የቁጥር እድገት ከትምህርት ጥራት ጋር አለመሆኑ አሳሳቢ መሆኑን ተናግረዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ የሚችል መመዘኛ አውጥቶ ድጋሜ መመዝገብ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን አትተዋል።

የተሟላ የትምህርት ተቋማት መረጃ መኖር የፖሊሲ ውሳኔዎችን ለመወሰን አስፈላጊ መሆኑንም አብራርተዋል። አያይዘውም ብቁ የሆኑ ተቋማትን ለማጥራት እና ብቁ ያልሆኑት ተቋማት ከገበያ እንዲወጡ ለማድረግ የተሟላ መረጃ መኖሩ እንደሚጠቅም ተናግረዋል።

መመዘኛዎቹም የሚሆኑት የተቋማቱ የአሠራር ሥርዓት፤ በተቋማቱ ውስጥ ያሉት የሰው ኃይሎች፤ የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያግዙ የሚችሉ አቅርቦት መሟላታቸው ናቸው ብለዋል።

የሚወጣውን የተቋማት መመዘኛን የማያሟሉ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ፈቃዳቸው እንደሚነጠቅ የተናገሩት አቶ ቸሩጌታ፤ መመዘኛውን በማያሟሉ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ወደ ተለያዩ መመዘኛውን ወደሚያሟሉ ትምህርት ቤቶች እንዲገቡ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

መመዘኛዎቹ በቅርብ ጊዜ ተጠናቀው ለሁሉም የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲደርስ ከተደረገ በኋላ፤ ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት የዝግጅት ጊዜ እንደሚሰጥ አብራርተዋል። በተሰጠው የዝግጅት ጊዜ መመዘኛውን አሟልተው ካልተገኙ ተጨማሪ ቀናት ይሰጣቸውና ከመመዘኛው በታች ሆነው ሲገኙ ፈቃዳቸው እንደሚነጠቅ ተናግረዋል።

# የባህላዊ ግጭት አፈታት ዘዴዎች ልምድ እየተዳከመ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የባህላዊ ግጭት አፈታት ዘዴዎች ልምድ እየተዳከመ መሆኑን የሰላም ሚኒስቴር አስታወቀ። ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ያላቸውን ክፍተት በመሙላት በተደራጀ መልኩ መጠቀም እንደሚያስፈልግም ጠቁሟል።



በሰላም ሚኒስቴር የግጭት አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ይርጋለም መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአገሪቱ እየተከሰቱ ያሉትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሲፈቱ የቆዩ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እየተዳከሙ ነው።

በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ ይርጋለም፤ የግጭት አፈታት ዘዴዎቹን ጥንካሬና ድክመት በጥናት በተደገፈ ሁኔታ መለየት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ይርጋለም ገለፃ፤ አሁን ላይ የባህላዊ ግጭት አፈታት ዘዴዎች ልምድ መዳከም እየታየበት ይገኛል።

ሰላም ሚኒስቴር ችግሩን ለመቅረፍ በአገሪቱ ያሉትን የባህላዊ ግጭት አፈታት መልካም ተሞክሮችን ለመቀመር የሚያስችል የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት በየክልሉ ያሉትን የባህላዊ ግጭት አፈታት ልምዶች መለየቱን አስታውቀዋል።

የባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር ተሰሚነታቸውና ተጽእኖ ፈጣሪነታቸው በመቀነሱ ውጤታማ እየሆኑ አይደለም ያሉት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፤ ተጽእኖ ፈጣሪነታቸውን ለመጨመር ጥልቅ ጥናቶችን በማከናወን ችግሮቻቸውን በመለየት፣ ከፖለቲካ አካላት ነፃ በማድረግና የበጀት ድጋፍ በመስጠት ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚቻል ተናግረዋል።

ከሁሉም ክልሎች ለተውጣጡ ለአገር ሽማግሌዎችና ለሃይማኖት አባቶች የአገር በቀል የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ምን መምሰልና በምን ዓይነት መልኩ ውጤት ማምጣት እንዳለባቸው ስልጠና መሰጠቱን አቶ ይርጋለም አብራርተዋል።

በግጭት አፈታት ሥርዓት የተሻለ ልምድ ባላቸው አካባቢዎች የተሠሩ ጥናቶችን በመለየት በጆርናል መልክ ለማሳተም ጥረት እየተደረገ ይገኛል ያሉት አቶ ይርጋለም፤ ከአዲስ አበባና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን በጉዳዩ ዙሪያ በቀጣይ አውደ ጥናቶች ይዘጋጃሉ ብለዋል።

ማህበረሰቡ የእራሱን ችግሮች በራሱ ባህላዊ ሥርዓት እንዲፈታ የአሠራርና ፖሊሲ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ይርጋለም፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማት ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ደረጃ የአሠራር ሥርዓትና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ባህላዊ ግጭት አፈታት ተቋማት ከመደበኛ የሕግ ተቋማት ጋር በቅንጅትና በመናበብ መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም አስረድተዋል።

አቶ ይርጋለም እንዳስታወቁት፤ በአሁኑ ወቅት የባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማትን ተሞክሮዎች የመለየት፣ የመቀመርና የማስፋት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

## የሰንበት ገበያዎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከነጋዴዎች በመረከብ በቀላሉና በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማቅረብ ያስችላሉ። ይህም የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

መንግሥት የኑሮ ውድነትን ለማርገብ ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል ብሎ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች መካከል አንዱ የሰንበት የገበያ ነው ያሉት ባለሙያው፤ ይህ ሥርዓት አምራቾችና ነጋዴዎች ምርቶችን ቀጥታ ለሸማቹ ከመቅረብ ባለፈ ለመንግሥት ግብር የማይከፍሉ እና ነፃ የንግድ ቦታ ስለተመቻቸላቸው የሚያቀርቧቸው ምርቶች ዋጋቸው ተመጣጣኝ እና አነስተኛ ነው። ይህም ለሸማቹ ኅብረተሰብ ምርቶችን በቀላሉና በአካባቢው በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸመት ያስችለዋል ብለዋል።

እንደ ዶክተር አረጋ ገለጻ፤ በሰንበት ገበያ በአንድ ቦታ ብዙ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በየአካባቢው ከማግኘት በተጨማሪም ሸማቹ ጊዜያቸው ያላለፈባቸው እና ባዕድ ነገር ያልተቀላቀለባቸው ምርቶችን ያገኛል፤ ከመጭበርበር ይድናል ፤ የሰንበት ገበያዎች ለአነስተኛ ነጋዴዎችም የመሸጫ ቦታ በቀላሉ በማግኘት ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁና እንዲሸጡ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፣ አቅማቸው እንዲጎለብትም የሚያደርግ ሥርዓት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሥርዓቱ ያለአግባብ ምርቶችን የሚደብቁና ዋጋ የሚጨምሩ ሕገወጥ ነጋዴዎችን ከመከላከል ባለፈ ሕገወጥ ነጋዴዎችን ወደ ሕጋዊነት መስመር እንዲገቡ በማስገደድ ማጭበርበርንና አላስፈላጊ መጨናነቅን በመቀነስ ትልቅ ፋይዳ አለው ያሉት ዶክተር አረጋ ፤ ከተጠቃሚው ብዛት አንጻር በቂ የሆነ የንግድ ቦታም ሆነ የምርት ስብጥር ያለው የሰንበት ገበያዎች የሉም፡፣ ይህን እያስተካከሉና የገበያዎችንም ቁጥር እየጨመሩ መሄድ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

መንግሥት የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የተለያዩ የመፍትሄ አማራጮችን የተጠቀመ መሆኑን ጠቁመው፤ በአሁኑ ጊዜም የሰንበት ገበያዎችን ተደራሽነታቸውን በማስፋት በቂ ምርቶችን ለሸማቹ ለማቅረብ መሠራት እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

በሰንበት ገበያ እየተገበያዩ ያገኘናቸው ወይዘሮ መአዛ አለባቸው እና አቶ ታሪኩ ሰይፈ እንደተናገሩት፤ የተጀመረው የእሁድ ገበያ በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ ያሉ የግብርና ውጤቶች ጥሩ አቅርቦት እንዲኖር አድርጓል፤ ዋጋቸውም ከሌሎች ሱቆች ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው። ምርቶችን በቀጥታ በዚህ መልኩ ማቅረብ መቻሉ በቀላሉና በተመጣጣኝ ዋጋ እንድናገኝና እንድንገበያይ አድርጎናል ብለዋል።

በእንቁላል ንግድ ላይ ተሰማርቶ ያገኘነው ወጣት እንዳለ ተመስገን፤ የሰንበት ገበያዎች ምርቶችን በቀጥታ ለሸማች ተደራሽ ከማድረጋቸውም ባለፈ የሥራ ዕድል እንደተፈጠረለት እና ብዙ ደንበኞችን ማፍራት እንደቻለ ገልጿል። ለወደፊትም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ምርቶችን ለማቅረብ እንደሚሠራ ተናግሯል።

ዜና

# በክልሉ የተከሰተውን የተላላፊ በሽታዎች ወረርሽኝ ለመግታት ጥረት እየተደረገ ነው

## • ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ አጎበር ተሠራጭቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የተከሰተውን የተላላፊ በሽታዎች ወረርሽኝ ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የክልሉ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ታምራት ቦጋለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በክልሉ በተለይ የወባና የኩፍኝ በሽታ በወረርሽኝ ደረጃ ተከስቷል።

የወባ ወረርሽኝ ስርጭቱን ለመግታትና ለመቆጣጠር ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ አጎበር እንደተሰራጨ ጠቁመው፤ በተጨማሪ ውሃ ያቆሩ ቦታዎች የማፋሰስና የኬሚካል ርጭት መከናወኑን ገልጸዋል።

የወባ በሽታ በክልሉ ሁሉም ዞኖች ከመከሰቱ በተጨማሪ በቤንች ሸኮ ዞን፣ በሸካና ኮንታ ዞኖች የስርጭት መጠኑ እንደጨመረ አስረድተዋል።

ባለፉት ሦስት ወራት ብቻ ከ30 ሺ. በላይ ዜጎች በወባ ወረርሽኙ መጠቃታቸውን ያስታወቁት አቶ ታምራት፤ በስድስት ወራት በበሽታው ከተጠቁ ሰዎች ጋር ሲነጻጸር በሦስት ወራት የተከሰተው በሽታ የ47 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል።

እንደ አቶ ታምራት ገለጻ፣ የወባ የህክምና መስጫ ግብዓቶች ችግሩ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማድረስ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል።

የወባ በሽታን ጨምሮ የኩፍኝና የኮሌራ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የባለሙያዎች ቡድን በማዋቀር በየዞኑ የመቆጣጠር ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ኅብረተሰቡ የአጎበር አጠቃቀሙን እንዲያሻሽልና የተሰራጨውን የወባ መከላከያ አጎበር በአግባቡ እንዲጠቀም እንዲሁም ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን እንዲያስከትቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

አቶ ታምራት እንዳስታወቁት፤ በክልሉ ዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ እና በቤንች ሸኮ ዞን ሸኮ ወረዳ የኩፍኝ በሽታ ተከስቷል። በእስካሁኑ ጥረት በሸኮ ወረዳ የተከሰተውን የኩፍኝ ወረርሽኝ መቆጣጠር ተችሏል።

በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ በአሁኑ ወቅት የኩፍኝ በሽታ ስርጭት እንዳይጨምር የክትባት እና የህክምና አገልግሎት ተጠናክሮ እየተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪ ከወራት በፊት በምዕራብ ኦሞ ዞን ሜኤኒት ጎልዲያ ወረዳ ተከስቶ የነበረው የኩፍኝ በሽታ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር መቻሉን ተናግረዋል።

ከወባና ኩፍኝ በሽታዎች ባለፈ የኮሌራ በሽታ በክልሉ አጎራባች አካባቢ ጎፋ ዞን መከሰቱን የጠቆሙት አቶ ታምራት፤ በሽታው ወደ ደቡብ ምዕራብ ክልል አካባቢዎች እንዳይዛመት በአጎራባች ወረዳ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የግልና የአካባቢውን ንጽህና በመጠበቅ ሊከላከል እንደሚገባም አሳስበዋል።

በክልሉ የኮሌራ በሽታ እንዳይከሰት ቅድመ-መከላከል ላይ በትኩረት እየሠራን ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በሽታው ቢከሰት እንኳን በፍጥነት መቆጣጠር የሚያስችል ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

በተለይ የኮሌራ በሽታ ተጠቂዎችን ለይቶ ለማቆየት የሚረዳ የማረፊያ ማዕከል ለማዘጋጀትና በቂ የመድኃኒት አቅርቦት እንዲኖር የሚያስችል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጤና ቢሮ ከክልሉ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በሰጠው መግለጫ በክልሉ የወባና የኩፍኝ በሽታዎች ወረርሽኝ መከሰቱንና የመቆጣጠር ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቋል።

---

# «ቃል፤ ተግባር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

29 ቀን 2015 ዓ.ም ለስድስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ይሆናል።

«ቃል፤ ተግባር፤ ትውልድ» በሚል መሪ ሀሳብ የተከፈተው የመጻሕፍት አውደ ርዕይ የንባብ ባሕልን ማጎልበትን ዓላማ ያደረገ እንደሆነ ተገልጿል። አውደ ርዕዩን በሚመለከት «ታሪክን ለትውልድ መሰነድ» በሚል ርዕስ የውይይት መድረክ ተካሂዷል። በውይይት መድረኩ ታሪክን በተሟላ አግባብ መሰነድ ለትውልድ ግንባታ ሚናው የላቀ መሆኑ በሀሳብ አቅራቢዎች ተነስቷል።

ከውይይት መድረኩ ጎን ለጎን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የተዘጋጁ ህትመቶችንና የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የጽሑፍ ሥራዎችን የሚዳስስ የመጽሐፍ አውድ ርዕይ ተከፍቷል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጻፉ መደመር፣ የመደመር መንገድና የመደመር ትውልድ መጽሐፍትን ጨምሮ የጽሕፈት ቤታቸው የጽሑፍ ሥራዎች ለሽያጭ ቀርበዋል።

«በጠቅላይ ሚኒስትር ቤተ ንባብ» በታሪክ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉ ባለሥልጣናት መጻሕፍት የሚቀመጡበት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። «በጠቅላይ ሚኒስትር ቤተ ንባብ» ላይ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ አንስቶ ለንባብ ያበቋቸው መጻሕፍት ቀርበዋል።

በአውደ ርዕዩ ማስጀመሪያ ላይ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ጳውሎስ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማኅበራዊ ዘርፍ አማካሪ ሚኒስትር ዲያቆን ዳንኤል ክብረት እና በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የፕሬስ ሴክሪታሪያት ኃላፊ ቢልለኔ ስዩምን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።

---

# «በአዲስ አበባ የተገነቡ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መኅብኘታቸውን ገልጸው፤ ፕሮጀክቶቹ የሕዝብን ችግር ለመፍታት ታስበው የተገነቡና አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን መረዳታቸውን ተናግረዋል።

በቀጣይ ሌሎች ከተሞች ላይ ተመሳሳይ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያነሳሱ ፕሮጀክቶች በመዲናዋ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸውን አቶ ዚያድ ጠቁመዋል።

በተቀመጠላቸው ጊዜና ጥራት ተጠናቅቀው ለሕዝብ አገልግሎት የበቁ የተለያዩ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች ተመልክተናል ያሉት ከንቲባው፤ ሁሉም የአገሪቱ ከንቲባዎች ተገኝተው ተገቢውን ልምድ የወሰዱበት ፎረም መደረጉን ገልጸዋል።

በመዲናዋ ከተገነቡ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች ልምዶችን በመውሰድ በጂግጂጋ ከተማ ተመሳሳይ ተግባራትን ለመፈጸም ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ ልምድ ተገኝቷል ብለዋል።

የአዳማ ከተማ ከንቲባ አቶ ኃይሉ ጀልዴ በበኩላቸው፤ እንደ አገር ብዙ ሀብትና መልማት የሚችሉ ዕድሎች እንዳሉ በአዲስ አበባ ከተከናወኑ ፕሮጀክቶች ተመልክተናል ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይም በሌሎች አገራት የሚታዩ ለሕዝብ ጥቅም ታስበው የተገነቡ ፕሮጀክቶችን በአገሪቱ መሥራት እንደሚቻል በመዲናዋ ማየት ተችሏል። በቴክኖሎጂ በመታገዝ ሁሉን አቀፍ ሥራዎችና ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች ለማከናወን የሚያግዝ ልምድ ተገኝቷል ብለዋል።

እንደ አቶ ኃይሉ ገለጻ፤ ፕሮጀክቶቹ ዘመናዊነት የታየባቸው በመሆኑ የአገሪቱን ልማት የሚያፋጥኑ ናቸው። እናቶችንና ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረጉ የምገባ ማዕከላት፣ የሥራ ዕድል የፈጠሩ ፓርኮችና ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች በመዲናዋ የተገነቡ ከብዙዎቹ በጥቂቱ ውጤታማ ፕሮጀክቶች ናቸው።

ሰው ተኮር በሆኑ ሥራዎች ረገድ በመዲናዋ በርካታ አስተማሪ ፕሮጀክቶችን ተመልክተናል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ የጊዜ አጠቃቀምን፣ እናቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉና የከተማን ገጽታ የሚያሳዩ አረንጓዴ ልማቶችን የተከናወኑ ፕሮጀክቶችን በከተማችንም ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ ነን ብለዋል።

በአዳማ ከተማ ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎች በመሥራት ላይ መሆናቸውን ጠቁመው፤ የከንቲባዎች ፎረም ከሕዝብ ከተገነቡ ፕሮጀክቶች ልምድ መውሰድ ያስቻለ መሆኑን አስረድተዋል።

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ከንቲባ አቶ ሀሩና አህመድ በበኩላቸው፤ በአዲስ አበባ ተሠርተው የተጠናቀቁና በመሠራት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ድሃ ተኮርና ውጤታማ የልማት ሥራዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተለይም በአጭር ጊዜ ተሠርተው የተጠናቀቁ የአቅመ ደካሞች የጋራ መኖሪያ ቤቶች ችግር ፈቺነታቸው ለሌሎች ከተሞችም ልምድ የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል።

እናቶች ደክመው በእንጨት ያዘጋጁት የነበረውን የእንጀራ ምርት ሂደት በኢንዱስትሪ የታገዘ እንዲሆን የሚረዳ ፋብሪካ በመዲናዋ መመልከታቸውን ጠቁመው፤ ለእናቶችና ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችሉ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች አመርቂ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ከንቲባዎች ፎረም ለሁለት ቀናት በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደ ሲሆን በመዲናዋ የተሠሩ የልማት ፕሮጀክቶችን ተጎብኝተዋል።

---

# ከታክስ ነፃ የሚገቡ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደሚያስፈልጉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ሀሳባቸውን ያጋራሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ዳዊት ሀዬሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት በፍራንኮ ቫሉታ አማካኝነት እንደ ፓስታ፤ ማካሮኒ፣ ዱቄት፤ የሕፃናት ምግብና መሰል የፍጆታ ምርቶች ከታክስ ነፃ እንዲገቡ ፈቅዷል። አብዛኛዎቹ ምርቶች ከውጭ የሚገቡ እንደ መሆናቸው መጠን ከታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ በፍራንኮ ቫሉታ በኩል ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን በነፃ እንዲገቡ ቢደረጉም ዋጋቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ለዚህ ደግሞ ምርቶቹ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት በውጭ ምንዛሬ አማካኝነት ከመሆኑ አንጻር የአገር ውስጥ የዋጋ ግሽበት ብቻ ሳይሆን የምርቶቹን ዋጋ መናር የሚጎዳው ከውጭ የመጣ የዋጋ ግሽበት( imported inflation) የሚባል በመሆኑ በምርቶቹ ዋጋ ላይ ጫና አሳድሯል ይላሉ።

የምርቶቹ በሚፈለገው መጠን ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና ዋጋቸው እንዳይቀንስ ያደረገው አንዱ ምክንያት ከምንዛሪ ጋር የተያያዘ ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ የማካሮኒ፣ ፓስታና ዱቄት ምርቶች በብዛትና በስፋት በግብዓትነት የሚጠቀሙት ስንዴን ነው። ስንዴን በብዛት የሚያመርቱት አገሮች በተለምዶ የዳቦ ቅርጫት የሚባሉት ሩሲያና ዩክሬን ናቸው፤ ነገር ግን አገራቱ በጦርነት ውስጥ ያሉ በመሆናቸው የግብዓት እጥረት ተፈጥሯል። የግብዓት አቅርቦት እጥረት ደግሞ አንዱ ለዋጋ ንረት ምክንያት ይሆናል። ይህም የምርቶቹ ዋጋ በሚፈለገው ልክ እንዳይቀንስና እንዳይረጋጋ አድርጎታል ነው ያሉት።

በሌላ በኩልም ምርቶቹ አገር ውስጥ እየገቡ ቢሆንም አገር ውስጥ ያለው የሰላም እጦትና አለመረጋጋት ምርቶቹን በማቅረብ ሂደት ውስጥ ዋጋቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። የጉልበት ዋጋ (labor coast) ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣበት ሂደት አለ። ይህም ያላደጉ አገሮችን ብዙ ጊዜ ዋጋቸው የሚተመነው በጉልበት ነው። በአሁኑ ወቅት ላይ ቁርስ፣ ምሳና እራት፣ እየጨመረ ከመሄዱ አንጻር የጉልበት ዋጋ መጨመሩ ዋጋቸው በተፈለገው መንገድ እንዳይሆን አድርጓል። ከትራንስፖርት ጋር የተያያዘው ዋጋ የጨመረበት ሁኔታ ስላለ ለምርቶቹ የዋጋ መናር አሉታዊ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን የምጣኔ ሀብት ባለሙያው በምክንያትነት ያነሳሉ።

ዶክተር ዳዊት እንደሚሉት፤ የገበያ ዋጋ የሚባሉት በአገር ውስጥም ተጨባጭ በሆነ መንገድ ጭማሪ ከማሳየት አንጻር በፊት ከነበረበት ሁኔታ ዋጋው ያልቀነሰበት ሁኔታ እየተስተዋለ ነው። ነገር ግን በፍራንኮ ቫሉታ አማካኝነት ከታክስ ነፃ ባይገቡ ኖሮ ዋጋው ምን ያህል ይንር ነበር ብሎ ማሰብም ተገቢ ነው። ፍራንኮ ቫሉታ ባይፈቀድ የምርቶቹ ዋጋ አሁን ካለው በላይ ከ25 እስከ 50 በመቶ ጭማሪ እንደሚያሳይ መገመት ይቻላል።

ከዚህ አኳያ በተወሰነ መልኩም የዋጋ ማረጋጋት አስተዋጽኦ እንዳለው መገመት ያስችላል። ለምሳሌ ከጎረቤት ስንዴን በስፋት ወደ ውጭ ገበያ ከሚያቀርቡ እንደ ግብጽና ሱዳን የመሳሰሉ አገራት ጋር ሲነጻጸር የስንዴ ዋጋ ሲታይ በእነዚህ አገራት ላይ ዜጎቻቸው መግዛት የማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል። በኢትዮጵያ የተፈቀደው ፍራንኮ ቫሉታም በተወሰነ መልኩም ቢሆን የምርቶቹ ዋጋ ከዚያም በላይ የናረ እንዳይሆን እገዛ እንዳለው ገልጸዋል።

በፍራንኮ ቫሉታ ከታክስ ነፃ በሆነ መልኩ መግባታቸው መልካም ነገር ነው የሚሉት ሌላኛው የፋይናንስና የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ኃይለመስቀል ጓዙ፤ ነጋዴው ማህበረሰብ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የሚገዛው በጥቁር ገበያ በሚያገኘው ምንዛሬ ነው። ይህም ማለት በባንክ ያለው የአንድ ዶላር ምንዛሬ 54 ቢሆንም እነሱ አንድን ዶላር ከመቶ ብር በላይ ገዝተው ዕቃዎችን የሚያስገቡ ነጋዴዎች ይኖራሉ። ይህም ለእነዚህ ምርቶች ዋጋ መናር አንዱ ምክንያት ነው። በሌላ በኩልም ዕቃዎቹ የሚጓጓዙበት ዋጋ መጨመሩም ሌላኛው ለዋጋቸው መናር ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዋል።

አቶ ኃይለመስቀል፤ የምርቶቹ ከታክስ ነፃ መደረግ በተወሰነ መልኩ የዋጋ ንረቱን መቀነስ ቢያስችልም ሙሉ በሙሉ ግን ዋጋውን መቀነስ አይችልም። ምክንያቱም ምርቶቹን ከታክስ ነፃ በሆነ መንገድ እንዲያስገባ የተፈቀደለት አካል ምርቶቹን ለማስገባት ምንዛሬ በጥቁር ገበያ ሊገዛ ይችላል። የጥቁር ገበያ ዋጋን አስቦ የሚደረግ ግብይት ሊኖር ስለሚችል የምርቶቹ ዋጋ የሚጨምርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በፍራንኮ ቫሉታ አማካኝነተ ከታክስ ነፃ ሆነው ገቡ ማለት ገበያውን አረጋጋ ማለት አይደለም ይላሉ።

የምርቶቹን ዋጋ በሚገባ ለማረጋጋት የአቅራቢውና የፈላጊው መጠን መመጣጠን መቻል አለበት ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ ይህ ካልሆነ ግን በራሱ ጊዜ የገበያ ዋጋውን እንዲንር ያደርገዋል። በተጨማሪም በዓለም ላይ ያለው የገበያ ሁኔታ ዋጋ እንዲጨምር አድርጓል። መንግሥት በዋጋው ላይ ጣልቃ መግባት የሚችልበት አግባብ ካለ ምርቶቹ የሚገቡበትና የሚሸጡበት ዋጋ መታወቅ አለበት ብለዋል።

በምርቶቹ ዋጋ ንረት ላይ ዋና መፍትሔው ከውጭ የሚገቡ የምግብ ሸቀጦችን በአገር ውስጥ ማምረት መቻል ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ዩክሬንና ሩሲያ ላይ ያለው መሬት ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። እናም መካናይዝድ የሆነ የእርሻ ልማት መሥራት ያስፈልጋል። የተትረፈረፈ ምርትን ማምረት መቻል ዋናው የዋጋ ንረቱ መፍትሔ ነው። ይህ ሲሆን ዶላር በጥቁር ገበያ ገዝቶ ከውጭ የማስገባቱ ሁኔታ ይቀራል።

አገር ውስጥ ምርትን መተካት ከተቻለ የውጭ ምንዛሬ እንደ ችግር አይነሳም፤ የአገር ውስጥ ገበያን በሚገባ ማረጋጋት ያስችላል። ታዲያ ይህ እንዲሆንና ምርትን ለማምረት ወሳኙ የሰላምና ደህንነቱ የተረጋገጠ አገር መገንባት ያስፈልጋል። የሰላም ዕጦት ገበያው እንዳይረጋጋ ያደርገዋል ።

እንደ አገር የተረጋጋ ሰላም ወሳኝ ነው። የሰላም እጦት ለዋጋ መናር ትልቅ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር የተረጋጋ ሰላም እንዲኖር በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ እየታየ ባለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ሳቢያ እንደ ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ ስንዴ፣ ፓስታና ማካሮኒና የመሳሰሉ መሠረታዊ ምርቶች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በነሐሴ ወር 2013 ዓ.ም. መፈቀዱ ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጽንፈኝነት ይወገድ!

የጽንፈኝነት አስተሳሰብ ሰለባ የሆኑ ግለሰቦች እና ቡድኖች የኖሩበትን ማኅበረሰብ ፣ ሀገራቸውን ፣ ከዚያም ባለፈ ዓለምን ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል። በቀደሙት ዘመናትም ሆነ ዛሬ ላይ ዓለማችን ያስተናገደቻቸውም ሆነ እያስተናገደቻቸው ያሉ አውዳሚ ጦርነቶች እና ግጭቶች በአንድም ይሁን በሌላ በዚህ የአስተሳሰብ ስንኩልነት የተፈጠሩ ናቸው።

ሁለቱን ዓለም አቀፍ ጦርነቶች ጨምሮ ባለፉት መቶ ዓመታት ዓለም ያስተናገደቻቸው ጦርነቶች ፤ በአብዛኛው የአስተሳሰብ መዛነፍ ባጋጠማቸው ጽንፈኛ ግለሰቦች ተጀምረው፣ የቡድን መንፈስ ተላብሰው ፣ በተዛቡ ትርክቶች ታጅበው የሰደድ እሳት ያህል በማኅበረሰብ ውስጥ ፈጥነው በመስራጨት ዓለምን ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን ያስከፈሉ ናቸው።

የአስተሳሰቡ ባለቤቶች /ጽንፈኞች/ አስተሳሰባቸው ማኅበራዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ፣ በተለይም ለስሜት ቅርብ የሆነውን ወጣቱን ትውልድ ከጎናቸው ለማሰለፍ የተለያዩ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ታሪካዊ የተዛቡ /የጥፋት ትርክቶችን በመፍጠር ፣ ለራሱና ለሀገሩ ነገዎች ተስፋ የሆነውን ትውልድ ባልተገባ መልኩ ለጥፋት ዳርገው እነሱም አስተሳሰቡ በወለደው እሳት ተበልተው አልፈዋል።

ይህ ዓለምን ከቀደመው ዘመን ጀምሮ እየተፈታተነ ያለ ስንኩል አስተሳሰብ ዛሬም ቢሆን ለሀገራት ፣ ከዚያም አልፎ ለዓለም ሰላም ትልቁ ስጋት ሆኗል። ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ መሰረት ተላብሶ ዓለምን እየተፈታተነ ያለው ጽንፈኝነት፣ አሁን ባለንበትም ዘመን በመካከለኛው ምስራቅ የተቀጣጠለው የጸደይ አብዮት መልኩን እንዲቀይር በማድረግ ሀገራትን እንደሀገር እንዳይቆሙ አድርጓቸዋል።

ዜጎቻቸው ተረጋግተው የተሻለ ሕይወት ይመሩ የነበሩ እንደ ሊቢያ፣ ሶሪያ እና ኢራቅን የመሳሰሉ ሀገራት እስከዛሬ ሊወጡት ወደማይችሉት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አዘቅት ጨምሯቸዋል፤ ዜጎቻቸውም ከስደት ባለፈ ጠባቂ እንዲሆኑ በማድረግ ብሄራዊ ክብራቸውን እንዲያጡ አድርጓቸዋል። ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሄ እንዳያገኙም እስከዛሬ ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖባቸዋል።

በኛም ሀገር ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ዘርን እና ሃይማኖትን ሽፋን አድርጎ እየተስተዋለ ያለው ጽንፈኝነት ሕዝባችንን በሁለንተናዊ መልኩ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል። የህዝባችንን ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር እሴቶችን ከመሸርሸር ባለፈ፣ በየዕለቱ በሚፈበረኩ አዳዲስ የጥፋት ትርክቶች እየታጀበ ሀገራዊ የስጋት ምንጭ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ሀገራችንንና ሕዝባችንን እየተፈታተኑ ካሉ አጀንዳዎች በስተጀርባ ገዝፎ የሚገኘው ጽንፈኝነት ፤ አሁን አሁን ወደ ከፋ ደረጃ ለመሸጋገር እየዳህ ስለመሆኑ ምልክቶች እየተስተዋሉ ነው። ቀደም ሲል በአማራ ክልልና በመከላከያ አመራሮች ላይ ፤ ሰሞኑን ደግሞ በአቶ ግርማ የሺጥላ ላይ ጽንፈኞች ያደረሱት ግድያን ጨምሮ ፤ በኃይልና በሽብር ወደ ስልጣን ለመምጣት እየተጓዙበት ያለው የጨለማ መንገድ ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ሕዝባችን ከተገነባበት መንፈሳዊ ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶች አኳያ ለጽንፈኝነት የተሰጠ ልብና አእምሮ ባይኖረውም ፤ አስተሳሰቡ በባህሪው የተለያዩ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን ጠልፎ በመውሰድ የጥፋቱ አቅም መገንቢያ አድርጎ የሚወስድ በመሆኑ፣ ሕዝባችንየዚህ ባህሪው ሰለባ እንዳይሆን ነቅቶ መጠበቅ ይኖርበታል።

በሃገራችን ካለው የብሔር ብሔረሰቦች እና የሀይማኖት ብዝሃነት አንጻር ፤በየትኛውም መንገድና መልክ የሚገለፅ ጽንፈኝነት ሊያስከፍለን የሚችለውን ያልተገባ ዋጋ ዛሬ ላይ ቆም ብለን ፣ በተረጋጋ አእምሮና በሰከነ መንፈስ ማየት ካልቻልን ፤የጥፋቱ አድማስ ሊሎች ሀገራት ለመከፈል ከተገደዱት የከፋ እንጂ ያነሰ እንደማይሆን ለማሰብ የሚከብድ አይሆንም ።

እንደ ጥላ ከሚከተሉን ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጀምሮ በየጊዜውመልካቸውን እየቀያየሩ ለውድቀታችን የሚተጉ ኃይሎች ፤ የዘመናት ምኞታቸው ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ከሁሉም በላይ ጽንፈኛ አስተሳሰቦች ማኅበራዊ መሰረት ሲይዙ መሆኑን ተረድተው በተቻላቸው ሁሉ እየሰሩ ነው።በዚህም ትናንት እና ዛሬ ላይ ያስከፈሉንና እያስከፈሉን ያለው ዋጋ ቀላል አይደለም።

ጽንፈኝነትን ይብቃ ብለን በቁርጠኝነት መነሳት ከቻልን ዛሬ ላይ የምናከብራቸውን መንድሞቻችንን ነፍስ ከመቅጠፍ አልፎ፤ነገ ላይ አባቶቻችን ከፍ ያለ የህይወት ዋጋ ከፍለው በብዙ ተጋድሎ ያቆዩልንን ሀገራችንን እንደሀገር ሊያሳጣን እንደሚችል ለአፍታ እንኳን ልንጠራጠር አይገባም። ስለሆነም ይህንን የሕዝብና የሃገር ጠላት ለማስወገድ መረባረብ ከሁሉም ኢትዮጵዊ የሚጠበቅ ሃገራዊ ግዴታ ይሆናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት

ፍሬሕይወት አወቀ

ጉርብትና ማለት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው አብሮ የመኖር ውጤት ነው። ‹‹ከሩቅ ዘመድ ይልቅ ቅርብ ያለ ጎረቤት›› የሚባለውም አብሮ በመኖር ውስጥ የሚፈጠረው ጠንካራ ግንኙነት ጥብቅና ከስጋ ዘመድ የሚልቅ በመሆኑ ነው። ጎረቤት ብትወድቅ ቀና የሚያደርግ፣ ጓዳ ጎድጓዳህን የሚያውቅ ክፍተትን የሚደፍን፣ መከራ ችግርን እንዲሁም ደስታ ሲገጥምህ በቶሎ ደርሶ አብሮ የሚጋራ ፈጥኖ ደራሽ ነው። ጎረቤት ‹‹ገመና ከታች›› ወይም ‹‹ገመና ሸፋኝ›› የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው።

በሰዎች ላይ በሚደርስ ማንኛውም መከራና ችግር ፈጥኖ ደራሹ ጎረቤት ነው። አሁን አሁን የአኗኗር ዘይቤያችን ለዘመናዊ አኗኗር ተጋልጦ የጉርብትና ሕይወት የተቀዛቀዘ ቢመስልም ጨርሶ አልጠፋም። እርግጥ ነው ዛሬ ካንዱ ቤት እንጀራ ታጥፎ ከሌላ ቤት ወጥ አይጨለፍ ይሆናል እንጂ ከላይ ከላይ በሆነ ፍቅር አልፎ አልፎም ቢሆን አብሮ መብላት መተሳሰቡና በክፉ መደራረሱ ግን አልቀረም። ዛሬ እናቶች የአቻ ጎረቤታቸውን ልጅ አዝለው ባያሳድጉም ‹‹ማሙሽ ደህና ነው ሚሚስ እንዴት ናት›› በማለት የጎረቤታቸውን ሰላም ውሎ ማደር መጠየቃቸው ግን አልቀረም። ሊቀርም አይችልም።

ትናንት ጠንካራ የነበረው የጉርብትና ትስስር ዛሬ እጅግ ሳስቶ ‹‹ጎረቤት ድሮ ቀረ›› ቢያስብልም የሳሳው እንዳይበጠስ፤ የተቀዛቀዘው እንዲሟሟቅ ቆም ብሎ ማሰብ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ከማሰብ ባለፈም መገለጫችን የሆነውን መረዳዳትና መተሳሳብ ጥብቅ በሆነው ጉርብትናችን መተግበር ያስፈልጋል። ምክንያቱም እኛ እኮ ኢትዮጵያውያን አብሮ በመኖር ለሌሎች መልካም ምሳሌ መሆን የቻልን ታላቅ ህዝቦች ነን። ግለኝነት በነገሰበት ዓለም ካለን ላይ ቀንሰን የምናካፍል፤ ጎረቤት ይሸተዋል ብለን የቀመስነው የምናቀምስ፤ እንግዳችንን እግር አጥበን ካልጋ የምናስተኛ፤ እኛ ደግሞ መሬት አንጥፈን የምንተተኛ ዓለም የመሰከረልን እንግዳ ተቀባይ ህዝቦች ነን።

‹‹...ያንተ ቤት ሲንኳኳ ይሰማል እኔ ቤት...›› እንዳለው ድምጻዊ የጎረቤት ችግር ችግራችን፤ የጎረቤት ደስታም ደስታችን፤ ይሆን ዘንድ የግድ የሆነብን እኛ ኢትዮጵያውያን ጎረቤት ተርቦ እኛ ጠግበን ማደር የማንችል፤ ጎረቤት ሲታመም እኛ ብርድ ብርድ የሚለን፤ የጎረቤት ሰላም ማጣት እንቅልፍ የሚነሳን በአንጻሩ ደግሞ የጎረቤታችን ሰላም መሆን ሰላም የሚሰማን ነን።

ይህ በጉርብትና ያዳበርነው ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነታችን ታድያ ግድግዳ ከሚለየን ጎረቤት አልፎ ከአገራት ጋር ባለን ጉርብትናም ስሜታችን አንድ ነው። ለአገራት ጉርብትና የነበረንና አሁንም ያለን ግንኙነት አገርኛ ከሆነው ጉርብትና የበለጠ ከሆነ እንጂ የሳሳ አይደለም። ምንም እንኳን የራሳችንን የማናስደፍር የሰውም የማንነካ ኩሩና ቆፍጣና ህዝቦች ብንሆንም ከጎረቤት አገራት ጋር አብሮና ተባብሮ በሰላም መኖርን አብዝተን እናውቅበታለን።

በሰላም አብሮ መኖርን በጉርብትና ያዳበረችው ኢትዮጵያ በታሪኳ ለገጠሟት ችግሮች ሁሉ የጠብ መነሻ ሆና አታውቅም። ለዚህም አብሮና ተባብሮ ተቻችሎ በመኖር የገነባቸው መልካም ዕሴቶቿ ምክንያት ናቸው። ያም ቢሆን ታድያ ገፍቶ ለመጣባት ጠላት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ሰላማዊ መንገድን ትመርጣለች። በተለያየ ጊዜ የገጠሟትን ችግሮች ስንመለከት ታድያ ችግሯን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት እስከመጨረሻው ጥግ በመጓዝ ለሰላም ዋጋ ትከፍላለች። እሳት ሆኖ የመጣውን ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት ውሃ ማድረግ ትችላለች።

አሁን አሁን ደግሞ ለሰላም ቅድሚያ ከመስጠት ባለፈ የውስጥ ችግሮቿን በውስጥ የመፍታት አቅሟን ከጉርብትና ወደ አገር ከአገርም ወደ አህጉር ከፍ ማድረግ ችላለች። ለዓለም የሚተርፍ የመቻቻልና የአብሮነት እሴት ያላት ኢትዮጵያ፤ በተለያዩ አካባቢዎቿ ለጸብ መድሃኒት የሆኑ ባህላዊ የእርቅ አይነቶች አሏት። አባቶች በዛፍ ሥር ተሰባስበው አጥፊውን ቀጥተው እርቀ ሰላም ከማውረድ ጀምሮ፤ ‹‹ዝቅ ያለ ከፍ ይላል›› እንዲል ቃሉ እርጥብ ሳር ይዘው ከመሬት ወድቀው ይቅርታና ምህረትን የሚጠይቁ፤ ለአገር ሰላም የሚተጉ ኢትዮጵያዊ አባቶች አሉ። እነዚህ ሁሉ መልካም እሴቶች ታድያ አብሮ በመኖር የዳበሩ በጉርብትና ተሰናስነው የመጡ ስለመሆናቸው የማይታበል ሃቅ ነው።

ኢትዮጵያ ዛሬ በትናንት መሰረቷ የሰላም ምሳሌ ከመሆን ባለፈ ‹‹የአፍሪካውያንን ችግር በአፍሪካውያን›› የሚለውን በተግባር ማሳየት ችላለች። ይህ ለሌሎች አፍሪካውያን እህትና ወንድሞች ምሳሌ መሆን የቻለ ታላቅ ተግባር ነው። ስለዚህ ‹‹...ሞያ ከጎረቤት›› እንዲሉ መላው አፍሪካውያን ኢትዮጵያ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት የወሰደችውን እርምጃ ቢወስዱ በብዙ ያተርፋሉ። በተለይም በአሁን ወቅት ጎረቤት አገር ሱዳን አሁን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ በሰላምና በፍጥነት መውጣት የምትችለው ‹‹የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› እንዲሉ አበው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የውስጧን ችግር በውስጥ አቅሟ መፍታት ስትችል መሆኑን የኢትዮጵያ መንግሥት በጽኑ ያምናል።

‹‹ያንተ ቤት ሲንኳኳ ይሰማል እኔ ቤት›› ነውና ነገሩ የጎረቤት ሱዳን ሰላም ማጣት ኢትዮጵያን እንቅልፍ የሚሰጣት አይሆንም። ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርበ ጎረቤት›› ነውና ነገሩ ከሌሎች አፍሪካ አገራት ይበልጥ የጎረቤት ሱዳን ህመም ለኢትዮጵያም ህመም ስቃይዋም ስቃይ በመሆኑ ቁስሏ ይጠዘጥዛታል። ለጉርብትና ትልቅ ዋጋ የምትሰጠው ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር ጥብቅና ጠንካራ ወዳጅ የሆነች ጎረቤት አገር ናት።

ኢትዮጵያና ሱዳን በመንግሥት መለዋወጥ ያልዋዠቀ ጽኑ ወዳጅና ጎረቤት አገራት ስለመሆናቸው ይነገራል። ታድያ ሱዳን ካጋጠማት ወቅታዊ ችግር እንድትወጣ የጉርብትና ትርጉሙን ጠንቅቃ የምታውቀው ኢትዮጵያ በየትኛውም ሁኔታ ከሱዳናውያን ጎን እንደምትሆን አረጋግጣለች። የኢትዮጵያ መንግሥታት ከአጼ ኃለስላሴ ጀምሮ አሁን እስካለው እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ መንግሥት ድረስ ሱዳን ያጋጠሟትን ችግሮች በሰላም እንድትፈታ ጉልህ ሚና መጫወታቸውን ታሪክ ይነግረናል።

ዛሬም ቢሆን ጎረቤት ሱዳን የገጠማትን የሰላም መደፍረስ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመነጋገርና በመወያየት መፍታት እንድትችል ኢትዮጵያ የጸና ፍላጎትና ዕምነት ያላት ስለመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ የሱዳን ወንድማማች ፓርቲዎች ወደ ሰላም ንግግር እንዲመለሱ ባቀረቡት ጥሪ የሱዳን ወንድማማች ፓርቲዎች ከግጭት አባባሽ ድርጊቶች ተቆጥበው የተፈጠረውን ግጭት በውይይት እንዲፈቱ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው በሱዳን ከተፈጠረው ግጭት ጋር በተያያዘ በአረብኛ ቋንቋ ባስተላለፉት መልዕክት የኢትዮጵያ መንግሥት በሱዳን ወንድማማች ፓርቲዎች መካከል የተፈጠረውን ግጭት በትኩረት እየተከታተለው እንደሆነም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሱዳን ወንድማማች ፓርቲዎች በመካከላቸው የተፈጠረውን ግጭት እንዲያረግቡ ባቀረቡት ጥሪ መሰረት በሁለቱ አካላት መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት እና የአፍሪካን ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ ለመስጠት አዲስ አበባ ሁሌም ቢሆን በሯ ክፍት እንደሆነ በመልዕክታቸው ጠቅሰዋል። ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ›› አበው ሱዳን ከጎረቤቷ ኢትዮጵያ በመማር የሰላምን መንገድ አማራጭ ብታደረግ መልካም ነው። እያልን፤ ሱዳን ሆይ! ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት ይበልጣልና ከጎረቤትሽ ኢትዮጵያ ተምረሽ ህዝብሽን ከጥፋት ታደጊ በማለት እናብቃ!

# ተጠየቅ

## «የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ያለዳኛ የሚካሄድ የእግር ኳስ ጨዋታ ሆኖ ቆይቷል»

ምህረት ሞገስ

**በቅርብ የተጀማመሩ ከጥቂቶቹ በስተቀር በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች የክልል ከተሞች እንዲሁም በአገሪቱ የግንባታ መጓተትም ሆነ መቆምን ማየት ከተለመደ ዓመታት ተቆጥረዋል። አንድ ግንባታ በሁለት ዓመት ይጠናቀቃል ተብሎ ከአስር ዓመት በላይ መፍጀቱ አስገራሚ አይሆንም። የጥራት ጉዳይም በተመሳሳይ መልኩ ተለምዷል። ይህ ለምን ሆነ? እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ምን እየተሠራ ነው? ስንል የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መስፍን ነገዎን ጠይቀን እንደሚከተለው ምላሻቸውን ይዘን ቀርበናል። መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን መቼ ተቋቋመ? ሲቋቋም ዓላማው ምን ነበር? ከሚለው ጀምረን ወደ መሠረታዊ ጥያቄዎቻችን እናምራ?**

**አቶ መስፍን፡-** የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን አሁን ያለውን ስም ይዞ የተቋቋመው በ2014 ዓ.ም ነው። የመንግስት አስፈፃሚ ተቋማትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው በአዋጅ ቁጥር 1263 የተቋቋመ ነው። ከዛ በፊት በለውጡ ማግስት አዋጅ 1079 ንዑስ 97 እንደዚሁ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን ለማዋቀር የወጣ አዋጅ ነበር። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ተብሎ እንደ አዲስ ተፈጥሮ ነበር። ከዛ በፊት ደግሞ ራሱን ችሎ በሚኒስቴር ደረጃ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተብሎም ነበር። እንደገና በአዋጅ 1079 ንዑስ 97 ባለስልጣን ሆኖ ራሱን ችሎ ወጣ።

ራሱን ችሎ የወጣበት ትልቁ ምክንያት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ያለዳኛ የሚካሄድ የእግር ኳስ ዓይነት ጨዋታ ስለነበር ነው። ያለዳኛ ቅድስ ጊዮርጊስ እና ቡና እግር ኳስ ቢጫወቱ አዲስ አበባ ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ቀውስ መገመት አያዳግትም። በኢንዱስትሪው ውስጥ የተሳካላቸው አገሮች ለዕድገታቸው ትልቁን ሚና የሚጫወትላቸው የኮንስትራክሽን ፖሊሲ፣ አዋጆች እና ስታንዳርዶች ላይ የተመሠረቱ ሆነው ኢንዱስትሪውን በመመራታቸው እና በመገራታቸው ነው።

ከለውጡ በፊት የነበረው የቁጥጥር ሥርዓት እጥረት ስለነበረበት፤ የኮንስትራክሽን ፖሊሲ ቢኖርም ቀውስ ውስጥ ነበርን። ከቀውሱ ለመውጣት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ቁጥጥር ባለስልጣን ተቋቋመ። በዚያን ጊዜ ሲቋቋም ዓላማው አሁን ከተቋቋመበት ዓላማ ብዙ የራቀ ባይሆንም የቁጥጥር መንገዱ ግን የተቆራረጠ ነበር። ለምሳሌ የኢነርጂ እና የውሃ ሥራዎች ቁጥጥር ሌላ ቦታ ነበር፤ መንገድ ደግሞ ሌላ ቦታ ነበር። ስለዚህ ሙሉ አልነበረም። በመሆኑም በ2014 ዓ.ም የሁለተኛው መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ሲደራጅ፤ እነኚህ እጥረቶች ተቀርፈው ራሱን በቻለ እና ሰብሰብ ባለ መልኩ በስትራቴጂ እንዲመራ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ የነበረው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ሆነ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ ተቋሙ በውስጡ በተለያዩ ተቋማት ስር የነበሩ ሥራዎች ያከናውናል ማለት ነው?**

**አቶ መስፍን፡-** አዎ! ለምሳሌ በውሃ እና ኢነርጂ ሥር የነበሩ የቁጥጥር ሥራዎች ወደ እኛ መጥተዋል። በኢነርጂ ባለስልጣን ሥር የነበረው የሲቪል ኮንስትራክሽን ቁጥጥር ወደ እኛ መጥቷል። የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ተብሎ የነበረው ሙሉ ለሙሉ የአስተዳደር ስራውን እርሱ ቢሰራም የቁጥጥር ሥራውን የሚሠራው ይህ ተቋም ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ባለስልጣኑ ምንም እንኳ በአዲስ መልክ ቢቋቋምም ቀድሞም ሲሠራ ነበር። ምን ያህል ዓላማውን እያሳካ ነው?**

**አቶ መስፍን፡-** አስቀድሜ ዓላማዎቹን ልዘርዝር። በአዲስ መልክ ከተቋቋመ ወዲህ አራት ዓላማዎች አሉት። አራቱም ዋነኛ ዓላማዎች መጨረሻቸው አንድን ግብ ማሳካት ነው። ግቡ ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን በቁጥጥር እየመሩና እየገሩ መፍጠር ነው። ይህንን ዋነኛ ዓላማ ለማሳካት አራት ንዑሳን ዓላማዎች አሉ። የመጀመሪያው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በጊዜ፣ በተያዘለት ዋጋና ጥራት የአካባቢ ደህንነትን ባረጋገጠ መንገድ መፈፀም አለመፈፀሙን መከታተል፣ መቆጣጠርና ማረም ነው።

ሁለተኛው ይህንን ሥራ ለማሰራት የሚያስችል በቂ ኮድ እና ስታንዳርድ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ ነው። እዚህ ላይ ኮድ እና ስታንዳርድ ያሰናዳል ማለት ነው። ሶስተኛው ኢንዱስትሪው ግብዓት ይኖረዋል። ግብዓቱ ደግሞ ከገበያ የሚገኝ ነው። ያንን የግብዓት ጥራት ማረጋገጥና በኢንዱስትሪው ውስጥ አልፎ የመጨረሻው ውጤት ማምጣት ነው። በዚህ ውስጥ ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ የሚውሉ መሠረተ ልማቶችን፤ ጥራት ማረጋገጥ ነው። የሕዝብና የአካባቢን ደህንነት ያረጋገጠ ሆኖ ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ግባችን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ አላማዎች የሚሳኩት መቼ ነው?**

**አቶ መስፍን፡-** በቀጣይ በትውልድ መካከል የሚሳኩ ናቸው። ሥራውም ሆነ ግቡ ውስን እና የሚቆም አይደለም፤ ዛሬ ያለው ፍላጎት ከአምስት ዓመት በኋላ ከሚመጣው ጋር የተለየ እና አዲስ ነው። ስለዚህ የሚመጡትን አዲስ ፍላጎቶች እየተከታተሉ፤ እነዚህን አራት አላማዎች ለማሳካት ይሠራል።

በጥያቄው ላይ የቀረበው አሁን ካለው ፍላጎት አንፃር ምን ያህል ተጉዛችኋል? ለሚለው ደግሞ አንደኛ እነዚህን አራት ሥራዎችን ለመስራት የተሰጠን ትልልቅ ኃላፊነቶች ሁለት ዘርፎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ዘርፍ ውስጥ የሚመደበው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ እና ስታንዳርድ ፍሬም ወርክን ማዘጋጀት እና መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ነው። የሌሉትን አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ማስገባት፤ ያሉትን ግን መተግበር ይችላሉ፤ አይችሉም የሚለውን ማየት ነው።

ሁለተኛው በመጀመሪያው ዘርፍ ላይ የሚገኘው መረጃ ነው። በየቀኑ የሚመጡትን መረጃዎች አደራጅቶ መያዝ ነው። ያለውን ትግበራ እና መረጃዎችን ይዞ፤ አደራጅቶ ትንተና አካሂዶ ለፖሊሲ፣ ለደንብ እና መመሪያ ማሻሻያ ግብዓት የሚሆኑትን ማሰባሰብ ነው። እዚህ ሥር ኢንደስትሪው ውስጥ የሚገቡ ማንኛውም አካላት የሚገቡት ተመዝግበው ነው። የምዘና እና የብቃት ማረጋገጫው በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስትቲዩት የሚሠራ ሆኖ፤ ምዝገባውን የእኛ ተቋም እየሠራው ነው።

ሌላው በሁለተኛው ዘርፍ ውስጥ ያለው ደግሞ የቁጥጥር ሥራ ነው። የቁጥጥር ሥራ ውስጥ መጀመሪያ የሚመጣው እነኚህ የተዘጋጁ የመለኪያ (ስታንዳርድ) ማዕቀፎች ትግበራ ቁጥጥር ነው። የተገዢነት ኦዲት ቁጥጥርን የምንሰራው በአገሪቷ አወቃቀር መሠረት ነው። በፌዴራል ደረጃ የሚሠሩትን እኛ እንተገብራለን። በክልል ደረጃ ደግሞ የክልሎቹ አደረጃጀቶች ይተገብሩታል፤ በከተማ አስተዳደር በማዘጋጃ ቤቶች ደረጃ ደግሞ የሕንፃ ሹሞች ይተገብሩታል። እንደ አዲስ አበባ ያሉ ሰፊ ከተሞች ላይ ደግሞ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ያሉ አስፈፃሚዎች ይተገብሩታል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ነገር የምትተገብሩት እንዴት ነው?**

**አቶ መስፍን፡-** አንደኛ በጥቆማ ኦዲት እናደርጋለን። ሁለተኛ በዕቅድ የተገዢነት ኦዲት ቁጥጥር ላይ ኮዶቹ እንዴት ተተገበሩ? የሚለውን እናያለን። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተጀምሮ የሚያልቅ፤ ቦታውን የሚቀይር እና በውል የሚፈፀም በመሆኑ ውዝግቦች ያጋጥማሉ። የእኛ ተቋም የኮንስትራክሽን ውዝግቦችን አማራጭ በማቅረብ ይፈታል። ይህ የሆነው ብዙ ፕሮጀክቶች የመዘግየታቸው ምክንያት አንዱ በውዝግብ እና በፍርድ ቤት ጊዜያቸው ስለሚበላ መሆኑ በመረጋገጡ ነው።

በተጨማሪነት ከከተሞች አስተዳደር ውጪ የሆኑ በፌዴራል የሚሠሩ ፕሮጀክቶች ለምሳሌ አገር አቋራጭ መንገድ እና የኃይል ማመንጫ ግድቦች የመሳሰሉት ከከተማ

አቶ መስፍን ነገዎ
የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር



ውጪ በመሆናቸው የከተማ ህንፃ ሹም የሚቆጣጠራቸው አይደሉም። ይህን የቁጥጥር ሥራ የምናከናውነው እኛ ነን። ስለዚህ የፕሮጀክት ቁጥጥር እንሠራለን። የፕሮጀክት ቁጥጥር ስንሠራ በየቀኑ ሳይሆን የምንሰራው ወሳኝ በሆኑ ደረጃዎች ላይ ያሉትን መረጃዎች (ዳታዎች) መሠረት አድርገን በመያዝ ቁጥጥር እንደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ያህል ሠራችሁ?**

**አቶ መስፍን፡-** መጀመሪያ በኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የነበርንበትን የሶስት ዓመት ታሪክ እናንሳ። ከዛ የአሁኑን የአንድ ዓመት ታሪክ እንዘርዝር። በሶስት ዓመት ውስጥ በዋናነት የንቅናቄ ሥራ ሠርተናል። ህግ ከማስፈፀም በፊት የሚመጣው አንዱ ህግን ለማሳወቅ ንቅናቄ መፍጠር ነው። ስለዚህ በተከታታይ ሶስት ዓመት በአምስት ክልሎች መድረኮችን በማዘጋጀት የሚመለከታቸው ባለድርሻዎችን አሳትፈናል። ያ ንቅናቄ በጣም ብዙ ግብዓት አምጥቶልናል። አንደኛው እታች ያሉ አደረጃጀቶች ከእኛ ሥርዓት አንፃር ያለው ምንድን ነው? የሚለውን ወስደናል። በሌላ በኩል ያሰብነውን ሥራ እና የእኛን ግብ ለማሳካት ወደ ሚመለከታቸው አድርሰናል።

አቅማችን አዲስ እንደተፈጠረ ተቋም በጣም ደካማ በመሆኑ የተወሰኑ ፕሮጀክቶችን ይዘን እያሳደግን እየሠራን ነው። በሶስቱ ዓመት መቶ በመቶ እየጨመርን ከ120 ፕሮጀክቶች በላይ አይተናል። ከ250 በላይ የህንፃ ፕሮጀክቶችን አይተናል። የውሃም ከ40 ፕሮጀክቶች በላይ አይተናል። ሌላው ትልቅ ስራ ሰርተን ውጤት አምጥተናል የምንለው ከ920 ፕሮጀክቶች በላይ ነበሩ። ከለውጡ በፊት ጀምሮ ያልተጠናቀቁ እና የቆዩ ነበሩ። ከ920ዎቹ ውስጥ 758ቱ የዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክቶች ናቸው። እነዚህ ፕሮጀክቶች ቆመው ነበር። የቆሙበት ምክንያት ምንድን ነው በማለት መረጃ በመሰብሰብ እና ትልቅ ጉባኤ በማዘጋጀት አማካሪ፣ ተቋራጭ እና የፕሮጀክቱን ማናጀሮች አካትተን አወያይተናል።

ፕሮጀክቶቹ የተነሳሽነት እና የአዋጭነት ጥናት ሳይደረግላቸው በስሜት የተጀመሩ ናቸው። ስለዚህ በግንባታ ጊዜ ውዝግብ ይኖራል። ይህ ይቅር ይባላል፤ ወይም ያልነበረ ነገር ይጨመር ይባላል። በዚህ ጊዜ ውዝግብ ይፈጠራል። እንዲያውም ከእነዚህ ውስጥ ወደ 20 ፕሮጀክቶች 80 በመቶ ለውጥ ተደርጎባቸዋል። የአገራችን የኮንስትራክሽን ገበያ ዋጋ በፍጥነት እያደገ በመሆኑ የእዛ ሰለባ ሆነዋል። እንዲያውም ብዙዎቹ በፍርድ ቤት የተያዙ ናቸው።

በደንብ እንነጋገር ከተባለ፤ ብረት በ17 ብር ውል የታሰረባቸው ለውጡ ሲመጣ የብረቱ ዋጋ 120 ብር ደረሰ። ውል በገቡበት መጠን መሔድ አልቻሉም፤ ስለዚህ ይህንን አጥንተን መንግስት የዋጋ ንረቱን የሚያካክስበትን መንገድ እንፍጠር በማለት ሦስት ወር ተኩል የፈጀ ጥናት አደረግን። ለገንዘብ ሚኒስቴር አቀረብን። ገንዘብ ሚኒስቴር ከፍተኛ በጀት ስለሚፈልግ ጊዜ ወሰደ፤ በመንገዱ ዘርፍ ወደ 71 ቢሊየን ብር ተጨማሪ ጠየቀ። በሕንፃው ዘርፍ ደግሞ ወደ 24 ቢሊየን ብር ተጨማሪ ብር አስፈለገ። ስለዚህ መንግስት ባለው ቁርጠኝነት የገንዘብ ማሻሻያውን ፈቀደ።

ከዛ በኋላ በዚህ ትልቅ ሥራ ከ758 ፕሮጀክቶች ከ400 የማያንሱት ግንባታቸው የቀጠለ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ 240ዎቹ ተጠናቀዋል። አሁንም በተቋራጮች፣ በአማካሪዎች እና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት አሁንም እያዘገሙ ያሉ አሉ። በእነዚህ ላይ ወደ ፊትም የምንሠራ ይሆናል።

በሌላ በኩል 18 ከተሞችን የተገዢነት የቁጥጥር ሥራ ሠርተናል። ሰፊ የኮድ እና ስታንዳርድ ትግበራ ክፍተቶች አሉ። ስለዚህ በሚቀጥለው የሶስት ዓመት ስትራቴጂ ውስጥ የምንተገብረው ይሆናል። ለምሳሌ ከአምስት ፎቅ በላይ መሠራት ያለበት በብረት መወጣጫ (ስካፎልድ) ነው። በእርግጥ በእንጨት መስራት ይቻላል። ነገር ግን በአሰራር ግድፈት ምክንያት የሠራተኞች ደህንነት አደጋ ላይ ስለሚወድቅ አዋጅ 624 ላይ በብረት መሆን አለበት ይላል። ይህ እየተፈፀመ ባለመሆኑ ስካፎልዶች ተንደው ሰዎች ላይ አደጋ ሲደርስ ይታያል። ይህ ሲነሳ ማዘጋጃ ቤቶችም ሆኑ አማካሪዎች አዲሶቹን ስታንዳርድ እና ኮዶችን ከመጠቀም ይልቅ የሚጠቀሙት የድሮውን እንደሆነ ማረጋገጥ ይቻላል። ስለዚህ ግንዛቤ መፍጠር ይፈልጋል። ያለበለዚያ አስገዳጅ ማድረግ እና የህግ ተጠያቂነትን ማስፈን የግድ ነው። ጉዳዩ የባለቤት፣ የተቋራጭ እና የአማካሪ ብቻ ሳይሆን የህዝብ ጉዳይም ነው። አንድ ዶክተር ቢሳሳት አንድ ሰው ይሞታል። አንድ መሃንዲስ ግን ቢሳሳት የሚፈጀው ብዙ ሰው ነው። ስለዚህ ጉዳዩ ከባድ መሆኑ መታወቅ አለበት።

ሌላው የተቋሙ ውጤት የምንለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አላሠራ ያለው ምቹ ሁኔታዎችን የማይፈጥሩ የህግ ማዕቀፎችን ማሻሻል ነው። የአማካሪ፣ የተቋራጭ እና የማሽነሪ ምዝገባ እንዲሁም የፕሮጀክት ምዝገባ አልነበረም። አሁን ግን ጀምረናል። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሥራዎች ከላይ የጠቀስኳቸውን ዓላማዎቻችንን ለማሳካት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል ናቸው።

# ተጠየቅ

ሌላው የዓሥር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ አለ። ይህ ዕቅድ በሶስት ዓመት የተከፋፈለ ሲሆን፤ አጠቃላይ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከተሰጠው መሰረታዊ ሥራዎች ውስጥ አምስቱ የእዚህኛው ተቋም ሥራዎች ናቸው። በእርግጥ ከአምስቱ በተጨማሪ በጋራ ከሌሎች ተቋሞች ጋር ተመጋጋቢ የሚሆኑ ሥራዎችም አሉ። የተወሰኑት ደግሞ በኛ ብቻ የሚሠሩ አሉ። የመጀመሪያው የቁልፍ አፈፃፀም አመልካች፤ ተብለው ብዙ ሥራዎችን የሚይዙ መመዘኛዎች አሉ። ይህ የሙስና ግንዛቤ መለኪያ (ኢንዴክስ) ነው።

ባለድርሻ አካላት ብዙ በመሆናቸውና የሚቃረን ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ በዓለምም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለሙስና የተጋለጠ ነው። በተለይ የቁጥጥር ዘርፉ ደካማ የሆነበት አገር፤ ሙስናው ሰፊና ሥር የሰደደ ነው። በዚህ ኢትዮጵያም ትነሳለች። ይህንን መቀልበስ ከቻልን የኢንዱስትሪውን ገፅታ እናሻሽላለን። ለዚህ አገር አቀፍ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ እና የዓለም መመዘኛዎች አሉ። ስለዚህ ይህንን ገፅ መቀየር አስፈላጊ ነው። ሌላው የኮንስትራክሽን ዘርፉን ተወዳዳሪነት መጨመር ነው። በአገር ውስጥ ተወዳዳሪ ሊሆኑ ይችላሉ። ከአገር ውጪም ተወዳዳሪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ የውጪዎቹ ወደ አገር ውስጥ መምጣታቸው በጣም ተለምዷል። ቻይናን አንዳንዶች የተዘዋዋሪ ቅኝ ግዛት እየተፈጠረ ነው እስከሚባል ድረስ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ስትሳተፍ ነበር።

ቻይናዎች መምጣታቸው ጥሩ ቢሆንም፤ መንግስት በህግ ማዕቀፍ ይህንን ኢንዱስትሪ ማብቃት እና ተወዳዳሪ አድርጎ የአገር ውስጥ ገበያን ድርሻ የመጨመር ኃላፊነት አለበት። በአገር ውስጥ ያለው የኮንስትራክሽን ገበያ ውስጥ ድርሻችንን መጨመር ተገቢ ነው። ሌላው ደግሞ በቀጣናው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ለእዚህ ዋነኛው ጉዳይ ቁጥጥር እና ስታንዳርድ ነው። ኬንያ ለመሔድ ቢሞከር መሰረታዊው ጥያቄ ስታንዳርድ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን የኮንስትራክሽን ተዋናኞች በስታንዳርድ እንዲበቁ ማድረግ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም።

አሁን ኢንዱስትሪው በተያዘለት ዋጋ እና ጥራት መጠን ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት ያቀርባል? የሚል ጥያቄ ከቀረበ ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አንፃር የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የሚሠራው የራሱ ድርሻ አለው። እኛ ደግሞ በቁጥጥር የምንሰራው የራሳችን ድርሻ አለን።

ሌላው ወሳኙ ከተያዘለት ጊዜ በላይ ምን ያህል ጊዜ ወሰደ የሚለው ነው። ለምሳሌ የሕዳሴው ግድብ የተያዘለት ጊዜ አምስት ዓመት ነው። ስለዚህ ጥያቄ የሚያስነሳው ኢንዱስትሪው ራሱ ጊዜውን ሲወስን ብቃት ነበረው? የሚለው ነው። እውነት የህዳሴው ግድብ በአምስት ዓመት ያልቃል ለማለት ይቻላል? ስንል ጠይቀን በደንብ ካሰላሰልነው ጊዜውን የገመትንበት መንገድ ጥራት አልነበረውም ማለት ነው። ስለዚህ አንደኛው የጊዜ ግምታችን ወደ እውነት የተጠጋ እንዲሆን ማድረግ ነው። አፈፃፀሙን በትክክል ገምተን በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ይጨርሳል? የሚለውን በትክክል ማሻሻል ነው።

ሌላው በተገመተው ወጪ ልክ ይጠናቀቃል? ለምሳሌ የሕዳሴው ግድብ የተያዘለት ሰማኒያ ቢሊየን ብር ነው። በትክክል ኢንዱስትሪው የገመተበት መንገድ ወደ እውነት የቀረበ ነው? ሲባል ጥያቄ ውስጥ ይገባል፤ ምክንያቱም ግምት ለእውነት የቀረበ ነው። የዛሬ አስር ዓመት የዓለም ዋጋ ምን ያህል ይሆናል? ብሎ መገመት መቻል አለበት። ከአዝሚያሚያዎች ተነስቶ መገመት አለበት። በእኛ አገር አሰራር እና በእኛ አገር ገበያ ብቃት ያለው የመገመቻ ሥርዓትን መገንባት የግድ ነው። እርሱን ካረጋገጥን በኋላ ደግሞ የመገመት ብቃትን ማረጋገጥ ነው። እናም በዛ ዋጋ የመጨረስ አቅምን መፍጠር ነው። እነኚህ አመልካቾች ናቸው። በእነዚህ አመልካቾች ውስጥ አስራ አንድ ጥናቶችን አስጠንተናል። በአገሪቷ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ስርዓት ባልያዘው የጊዜ ግምት ከ157 በመቶ በላይ መፋለሶች አሉ፤ የዋጋም ጉዳይ ከዚህ በላይ ነው። በተለይ አሁን ደግሞ ጠዋት እና ማታ የግብዓት ዋጋ በሚቀያየርበት ወቅት ከዛ በላይ ይሔዳል ማለት ነው። ስለዚህ ወደ ፊት ከዚህ ተነስተን የዋጋም ሆነ የጊዜ ግምት ሥርዓታችን በዚህ ያህል ተሻሽሏል እንላለን።

ከዓላማችን አንፃር ሲቃኝ፤ ሥራዎች ከዓላማችን ጋር የተያያዙ ናቸው። የሶስት ዓመቱን ገምግመን በፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ካሉት ዘርፎች የከተማ እና መሰረተ ልማት ከገቢዎች ቀጥሎ ያለ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል። እንደተቋም ግን ስናይ በተለይ ከአሰራር እና ሙስናን ከመከላከል አንፃር በአፅንኦት መሥራት አለብን



**አቶ መስፍን ነገዎ**
**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**

ብለናል። በአጠቃላይ ግን ሙስና ላይ፣ የአገር ውስጥ እና የቀጣናው ተወዳዳሪነት፣ የጊዜ እና የዋጋ ግምት ላይ እን ሠራለን።

**አዲስ ዘመን፡- በዋናነት ግን ግንባታዎች የሚዘገዩበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ መስፍን፡-** ከምክንያቱ በፊት ባለድርሻ አካሉ ማን ነው? የሚለው በደንብ ማየት ይፈልጋል። ሁሉም የድርሻውን ማግኘት አለበት። ባለድርሻ አካላት የሚባሉት ብዙ ቢሆኑም ዋነኛዎቹ አራት ናቸው። አንደኛው የፕሮጀክቱ ባለቤት ነው። እርሱ ራሱ በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው ገንዘቡን የሚበጅተው አለ። ለምሳሌ መንገዶችን ብናይ የዓለም ባንክ ነው። የዓለም ባንክ በአንዴ ገንዘቡን አይለቅም፤ በራሱ መስፈርት እየመዘነ ግንባታውን ሲያምንበት ገንዘቡን ይለቃል።

ሌላው የሥራው ባለቤት፣ ተቋራጩ እና አማካሪው አሉ። ሁሉም የየራሳቸው ሚና አላቸው። ከእነዚህ ውጪ የሆኑ ካለእነርሱ ግንባታው የማይሳካ፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች አሉ። አቅራቢዎች፣ የማሽን አከራዮች፣ የፋይናንስ ተቋሞች፣ ዋስትና የሚሰጡ ኢንሹራንሶችም የየራሳቸው ሚና አላቸው። ለምሳሌ አቅራቢው ለኮንትራክተሩ ውል ገብቶ ካላቀረበ ተቋራጩ ሽባ ይሆናል።

በተጨማሪነት ደግሞ እንደእኛ ያሉ የመንግስት ተቋማት የቁጥጥር ባለድርሻዎች አሉ። ፈቃድ የሚሰጡ፣ የግንባታ አካላቶችን የሚቆጣጠሩ፣ የሚከታተሉ እና ኢንዱስትሪውን በፖሊሲ የሚመሩ አሉ። እነዚህ አራቱም የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። ከጥያቄው አንፃር ሲታይ በፋይናንስ ችግር የቆሙ አሉ። ለምሳሌ ወደ አቃቂ ያለው መንገድ ፕሮጀክቱ ፋይናንሱን አቆመ። መንገዱ ወዴት ይሂድ? ውዝግቡን ጨርሶ ለመፍታት እስከ ዛሬ ቆየ። አሁን መተረቻ ሆኗል። ችግሩ ግን የፋይናንስ ነው።

ብዙዎቹ የመንግስት ሕንፃ ፕሮጀክቶች ዩኒቨርሲቲዎች የቆሙት በውዝግብ ነው። የይገባኛል ጥያቄዎች አሉ። አንደኛ የይገባኛል ችግር ምንጩ አማካሪ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከላይ እንዳልኩት አዋጭነቱ በደንብ ስለማይጠና ሌላ ያልነበረ ፍላጎት ይወለዳል። ግማሾቹ ወደ ፍርድ ቤት ይሔዳሉ። ለምሳሌ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ወደ አስራ አራት ህንፃ ከአስራ ሁለት ዓመት በላይ ዘግይቷል። ይህ የሆነው በፍርድ ቤት ምክንያት ነው። አንድ ብሎክ በትንሹ 500 ተማሪ ይይዝ ነበር ቢባል በአስራ አራት ሲባዛ በአስራ ሁለት ምን ያህል የአርሶአደር ልጆች ዕድል እንደተመናመነ ማሰብ ይቻላል። ስለዚህ በሚፈጠር ውዝግብ የመጡ ችግሮች ብዙ ናቸው።

ሌላው ደግሞ ከዋናው ኮንትራክተር ውጪ ያሉ ሌሎች ንዑሳን ኮንትራክተሮችን የተመለከተ ነው። የህንፃውን ሊፍት ኮንትራክተሩ ለንዑስ ኮንትራክተር ኮንትራት ይሰጣል። እንደገና ሊፍት ለማስመጣት ኤል.ሲ ይጠየቃል፤ ዶላር ያፈለጋል፤ የዶላር እጥረት ሁለቱንም ተቋራጮች ይይዛል። በተለይ ብዙ መንገዶች እና ትልልቅ ፕሮጀክቶች የቆሙት በውጭ ምንዛሬ ችግር ነው። ሌላው የቁጥጥር ችግርም አለ። በጊዜ ይህንን አስተካክሉ ስለማይባል መንግስትም ሆነ ፕሮጀክቱ ተጎጂ ይሆናሉ።

ለምሳሌ ወደ ፍርድ ቤት ከመሔድ ይልቅ ተቆጣጣሪው አማራጭ ሥርዓት ቢኖረው ወዲያው ችግሩ ይፈታ ነበር። ፍርድ ቤት ለማጣራት የሚወስደውን ጊዜ ያሳጥር ነበር። ስለዚህ በእነኚህ ባለድርሻዎች ያለው እጥረት በሙሉ ብዙ ፕሮጀክቶች እንዲቆሙ አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ ቢጠቅሱትም በደንብ አብራሩልኝ። ምን ያህል ፕሮጀክቶች ቆሙ? በእናንተስ ምን ያህል ተጠናቀቁ?**

**አቶ መስፍን፡-** 920 አካባቢ ናቸው። እነዚህን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው ከለውጡ በፊት የነበሩ እና ከለውጡ በኋላ ያሉ እንበላቸው። ከለውጡ በፊት የነበሩ በተለይ በሁለት ዓመት ይጠናቀቃሉ ተብለው የነበሩ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑት ተጠናቀዋል። አንዳንዶቹ በሲሚንቶና ብረት በግብአት እጥረት የተጓተቱ ናቸው። ይህ የዋጋ ማስተካከያ ስለተፈቀደ፤ እርሱን በስራ ላይ ያሉ አማካሪዎች እና ተቋራጮች ያሉበት ፈጥነው ወደ መጠናቀቅ ደርሰዋል። አሁንም ግን ጭቅጭቅ እና ውዝግብ ላይ ያሉ ተጓትተዋል። በእኛ ቁጥጥር ስር ያሉ ከ258 በላይ የሚሆኑት ግን ግብረመልስ ተሰጥቷቸው፤ የግብረ መልሱ ክትትል እየተደረገ ነው። 240ዎቹ ተጠናቀዋል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ግንባታዎቹ በጊዜ ባለመጠናቀቃቸው አገሪቱ ምን ያህል ተጎድታለች ይላሉ? ይህንን አስጠንታችኋል?**

**አቶ መስፍን፡-** እውነቱን ለመናገር አላስጠናንም። ነገር ግን ካለው የዋጋ ንረት እና የዘገዩበትን ጊዜ ደምረን ስናያቸው በእርግጠኝነት ከተያዘው በጀት በላይ አስር እጥፍ እና ከዛ በላይ ጨምረዋል። ለምሳሌ ተቋሙ ያለበት እንፃ ለግንባታ ሲጀመር 400 ሚሊየን ብር ይፈጃል ተብሎ የተጠናቀቀው በዛው ብር አካባቢ ነው። ትንሽ ቢዘገይ ኖሮ ግን ከ4 ቢሊየን ብር በላይ ይፈጅ ነበር። ስለዚህ እነኚህ ፕሮጀክቶች ዘገዩ ቢባል አንዷን የብረትን ወጪ ስናይ በኪሎ በ17 ብር ሂሳብ የገቡ ውል የተያዘላቸው ናቸው። ዛሬ የብረት ዋጋ ወደ 140 ብር አካባቢ ደርሷል። ቢዘገይ መንግስት በዚህን ያህል ይከስራል ማለት ነው።

በእርግጥ መንግስት መሠረተ ልማት የሚገነባው ለማትረፍ አይደለም። ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማዋል ነው። ስለዚህ ብዙ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ቢጠናቀቁ ይኖራቸው የነበረ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የታቀደላቸውን ያህል ይሆን ነበር። መንገድ ከሆነ ከአርሶ አደሩ ጋር፣ ከማዕድን ጋር አጠቃላይ ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጋር ይያያዛል። ትምህርት ቤት ከሆነ ደግሞ ነገ ኢትዮጵያን ከሚረከብ ትውልድ ጋር የሚያያዝ ነው። የአንድ ኮንስትራክሽን መቋረጥ ጉዳቱ ብዙ ነው። ያስከተለውን ጉዳት በሚመለከት በሚቀጥለው ዓመት ለማስጠናት እንሞክራለን።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ እንደዚህ ተመሳሳይ ተደጋጋሚ እና ብዛት ያለው የግንባታ መቆም እንዳይኖር የቆሙትም ሙሉ ለሙሉ እንዲጠናቀቁ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ መስፍን፡-** መንግስት ሁለት አቅጣጫዎችን ይዟል። አንደኛው ፕሮጀክቶች በስሜት ዝም ብለው ወደ ሥራ እንዳይገቡ እና በስሌት እንዲሰራ አቅዷል። ያንን ስሌት ማን እንደሚሠራ ባለቤት ሰጥቷል። ለምሳሌ ለፕላን እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር የተነሳሽነት ክፍሉን እና የአዋጭነት ጥናት ተካሂዶ ፕሮጀክቱ ከታመነበት ይፀድቃል። ፕሮጀክቱ ሲፀድቅ ተቋማችን ይመዘግባል። ወደ ዲዛይን ሲገባ እኛ ዲዛይኑን እንከታተላለን። ምክንያቱም መጨረሻ ላይ ፕሮጀክቱ ላይ ችግር የሚፈጠረው በቅድሚያ ዲዛይኑ ላይ ችግር ሲኖር ነው። ስለዚህ ዲዛይኑ በደንብ ይሠራል።

ሌላው በጨረታ ጊዜ የሚመጡ ሁለት ትልልቅ ጥፋቶች አሉ። በጨረታ ጊዜ አንደኛው ዋጋ ሰብሮ ይገባና መጨረስ ያቅተዋል። ስለዚህ በአነስተኛ ዋጋ የሆነበትን ምክንያት ዘርዝሮ ማስረዳት ይጠበቅበታል። ይህንን ሌላው ዓለምም የሚጠቀምበት ነው። ለምሳሌ የሲሚንቶ ዋጋ በገበያ ላይ 1ሺህ 200 ብር ሆኖ እርሱ በ200 ብር ገዝቼ እሰራለሁ ካለ ምን ሊያተርፍ ነው? ስለዚህ አይሰጥም። በዲዛይን ጊዜ ድብቅ ትርፍ ይኖረዋል ማለት ነው። በአርቴፊሻል ዋጋ ይተክልና በውዝግብ የሚበላውን ገንዘብ ያስባል።

የግዢ አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ታይቶ ወደ ምክር ቤት ሄዷል። በአዋጅ እና በህግ የሚመለሱ አሉ። የሙስና ጉዳይ በጥብቅ ዲስፕሊን ከተመራና ወቅታዊ ውሳኔ ከተሰጠ እንደዚህ ዓይነት መዘግየቶች ዕድላቸው ትንሽ ይሆናል። ውዝግቦች ቁጥራቸው ያንሳል። ውዝግቦች ሲኖሩም አማራጭ ውዝግቦችን ለመፍታት በተቋማችን ራሱን የቻለ ይህንን ሥራ ብቻ የሚሠራ የሥራ ክፍል እየተደራጀ ነው። በቀጣይ ውዝግቦች እየተቀጩ የሚሄዱበት ሥርዓት ይኖራል። ይህ ደግሞ ያደጉት አገሮችም የተጠቀሙት ነው። ተቋራጮችም ሆኑ አማካሪዎች ክልል ላይ መጥፎ ሥራ ሰርተው የፌዴራልን ወይም ፌዴራል ላይ መጥፎ ሥራ ሰርተው ከክልል ክልል የሚንሸራሸሩበት ዕድል አይኖርም።

በስርዓት ዳኛ ኖሮ የሚጫወት ይጫወታል፤ መውጣት ያለበት ይወጣል። ቻይና እና ህንድም በዚሁ መልኩ ተመሳሳይ ነበር። ቻይና የኮንስትራክሽን ዕድገት በሶስት ተከፍሎ ሲታይ የመጀመሪያው ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ ነው። በኢትዮጵያም የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታ (ሮድ ማፕ) ተዘጋጅቷል። ችግሮች የሚቀረፉት እና ወደ ትክክለኛው መስመር የሚገቡት በሁለተኛው ዘመን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የቀሩትን ለማጠናቀቅ ምን ዕቅድ ተይዟል?**

**አቶ መስፍን፡-** አሁን መንግስት የያዘው አቅጣጫ ሁለት ነው። አንደኛው ፕሮጀክቶቹ ተለያይተው ይቀመጡ። ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ እና ቁርጠኝነት የሚያስፈልጋቸው በቅድሚያ ይለቁ የሚል ነው። ሌሎቹ ግን ለትንሽ ጊዜ ቆም ብለው በተለይ የበጀት ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት በሚችሉበት ጊዜ ይሠራሉ። አንዱ ይህ ነው። አዲሶቹ ግን እንደነዛኞቹ ሰለባ እንዳይሆኑ ቁጥጥር ስለሚደረግ ብዙ ችግር አያጋጥምም ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- መገለፅ ያለበት ቀረ የሚሉት ካለ ?**

**አቶ መስፍን፡-** መገናኛ ብዙሃን እንደአራተኛ መንግስት የሚቆጠሩ ናቸው። ከጎናችን ሆነው ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው። አንደኛው መሰል ተቋማትን መጠየቅና ሌሎችም ባለድርሻ አካላትን የፕሮጀክት ባለቤቶችን፣ ተቋራጮችን እና አማካሪዎችን እየፈለፈሉ ማጋለጥ ከቻላችሁ ህዝቡ ራሱ ጥራት፣ ዝርፊያም ሆነ ደህንነት ላይ ጠያቂ ከሆነ እና ከተባበረ ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ መሆን ይቻላል። ስለዚህ መገናኛ ብዙሃን እንዲተባበሩን ጥሪዬን አቀርባለሁ። ቁጥጥር የአንድ አካል አይደለም። ህዝብም መተባበር አለበት። ህዝቡም ከተባበረ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን በማሳካት ውጤታማ እንሆናለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ መስፍን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ብዙ ተከፍሎበት የቆየልንን ሰላም ብዙ ከፍለን ልናጸናው ይገባል

በጋዜጣው ሪፖርተር

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሀገርን በማጽናት ሂደት ውስጥ ለነጻነታቸው በበርካታ ጦርነቶች ውስጥ አልፈዋል። በእያንዳንዷ የጦርነት ወቅትም ከወታደር እስከ ሰላማዊ ዜጋ በወርቅ መዝገብ ሊሰፍር የሚገባውን ተጋድሎ ፈጽሟል። የዚህ ምስጢር ደግሞ ቅኝ ለመገዛት ፤ ላለመወረርና ላለመንበርከክ ያለ ቁርጠኝነት ብቻ ሳይሆን የሰላምን ዋጋና ሰላምን ለማረጋገጥ ብዙ መስዋእትነት መክፈል የሚጠበቅ መሆኑን በመረዳታቸው ነው።

ይሄ የአያት ቅድመ አያቶቻችን ታሪክና ገድል ነው። የዛሬዎቹ እኛ ደግሞ ይሄንን ብንችል የራሳችንን አዲስ ገድል መጻፍ፤ ባንችል ደግሞ ይሄንን አስጠብቆ ለቀጣዩ ማኖር ይጠበቅብናል። ለዚህ ደግሞ የታሪክ ባለቤትነቱን የማኖርም፣ የቀደምቶቹን ታሪክ ብሎም ያስጠበቁለትን ሀገር በነጻነትና በሰላም የማስቀጠም አስጠብቆ የማዝለቅም ኃላፊነቱ ከመቼውም ግዜ ባልተናነሰ ትግልን ይጠይቀዋል። ለዚህ ደግሞ የራቀውን ታሪክ ለታሪክ ሰናጆች ትተን የኢትዮጵያ ወርቃማ ልጆች እንደ አንድ ልብ መካሪ.. እንደ አንድ አንደበት ተናጋሪ ... ሆነው የዛሬ 87 አመት የፈፀሙት ተጋድሎ ለዛሬው ትውልድ ቅርብ ምስክርም አስረጅም አድርጎ ማየት ይቻላል።

ወቅቱ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን መላው አለም በሁለተኛው የአለም ጦርነት የተጠመደበት ነበር። ጠንካራና ሀያላን የተባሉት የአውሮፓ ሀገራት ሳይቀሩ ብዙ የማይሽር ጠባሳን አስቀምጠው ያሳለፉበትም አጋጣሚ ነበር። እኛም ከቀናት በኋላ የምናከብረው የድል በዓላችን ዛሬ ያለው መላው ኢትዮጵያዊ አያት ቅድመ አያቶቹ ዛሬ እንዲኖረው ላሰቡት ሰላም ለትውልድ ሲሉ የከፈሉለት ዘመን አይሽሬ መስዋእትነት ውጤት ነው።

ወቅቱ የሚታወሰው ወራሪው የጣሊያን ጦር አገር የተቆጣጠረ ያለ በመሰለው ወቅት ፈላጭ ቆራጥ በመሆን በየዱር በገደል የሚዋጉትን አርበኞች የተበቀለ በሚመስል መልኩ ህዝብ እየጨፈጨፈ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሰላም ሲነሳ የነበረበት ነው። በዚህ ወቅት እያንዳንዱ አርበኛ ኢትዮጵያዊ መሞት ፈልጎ ሳይሆን ለሰላም መስዋእትነት መክፈል የግድ ይል ስለነበር ጉሮሮ ለጉሮሮ እየተናነቀ በከፋ መስዋእትነት የሀገሩን ነጻነትና ሰላም ማረጋገጥ ችሏል።

በአምስት የትግል ዓመታት በወራሪው ኃይል የተሰዉ ኢትዮጵያውያን ያን ሁሉ መከራ የተሸከሙት የኛን ሰላምና ነጻነት ለማስጠበቅ ነበር። ልፋታቸውም ውጤት አግኝቶ ዛሬ ላይ እንድንደርስ አብቅተውናል። ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ ለወረራ በገባ ኃይል ከሚፈጸም ጭፍጨፋ እና የሰላም እጦት ነጻ መውጣት ብንችልም፤ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ እኛ ኢትዮጵያውያንና ሀገራችን ኢትዮጵያ የምንፈልገውን ሰላም አስጠብቀናል ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ የለም። ምክንያቱም ዛሬም ድረስ ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ የሚከሰቱ ፖለቲካዊ ችግሮች በተለያዩ ግዜያት እየተከሰቱ እየፈተኑንም ብዙ እያስከፈሉንም ይገኛል።

ይሄ ደግሞ ለውጪ ጠላት በአንድ ጸንቶ የቆመ ማንነታችን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ጠላትን ካስወገደ በኋላ በአንድነቱ ጸንቶ የቆመበትን እሴት በመተው ለልዩነቶቹ ቦታ በመስጠቱ ምክንያት የተፈጠረ ነበር። በእነዚህ ልዩነቶች ደግሞ እርስ በእርስ ተገፋፍተናል፤ ጦር ተማዝዘንም ዋጋ ከፍለናል።

ሆኖም እነዚህ በውስጥ የገጠሙን አለመስማማቶች በሙሉ ሁሉም ሊባል በሚያስደፍር ደረጃ ከጦርነት ማግስት በድርድርና በስምምነት የተጠናቀቁ ናቸው። ለምን ቢሉ፣ እነዚህ አለመግባባትና ግጭቶች ቀድሞውኑ ከእልህ ወጥቶ መመካከር መነጋገር ቢቻል ኖሮ ዶላር የሚተፉ ጠብመንጃዎች የንጹሀንን ነፍስ ሳይነጥቁ... አካል ሳያጎድሉና ንብረት ሳያወድሙ በቀሩ ነበር።

ልዩነቶቻችን ደግሞ መገዳደል የሚያደርሱ ሳይሆኑ በወቅቱ በአግባቡ ቢያዙ በሀሳብ የበላይነት የሚፈቱም ነበሩ። ሌላው ቀርቶ ይህን የድል ቀናችንን «መጋቢት ሃያ ስምንት» ይሁን ወይንስ «ሚያዚያ ሃያ ሰባት» በሚል ብዙ ተወዛግበን በተለያዩ የአስተዳደር ዘመናት በተለያዩ ቀናት ስናከብረው መቆየታችን የታሪካችን አንድ ክስተት መሆኑን ለማስታወስ እፈልጋለሁ።

ይህ የሃሳብ ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው፤ ቁምነገሩ የሃሳብ ልዩነቶቹን በመነጋገር ማረቅና ማስማማት መቻሉ ነው። እዚህ ላይ ዛሬ ሰላም ናቸው ብለን ከሰላም ኗሪ ህዝቦች ተርታ የመደብናቸው ሀገራትም ቢሆኑ የውስጥም ሆነ ውጫዊ ችግር የለባቸውም ማለት አይደለም። በየትኛውም ሀገርም ሆነ ህዝብ ውስጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎችና የሚከሰቱ አለመግባባቶች እንዳሉ ይታወቃል። ልዩነቱ ግን ያለው እነዚህ ሀገራት ያሉባቸውን ልዩነቶችንም ሆነ አለመስማማቶች ወይንም ጥያቄዎች የሚያስተናግዱ‍ቸው ሰላማቸውን በማያደፈርስ የእለት ከእለት እንቅስቃሴያቸውን በማያውክ መልክ ነው። ምክንያቱም ሰላም ካለ ሁሉንም ነገር ለማድረግ ስለሚቻል ነው።

አሁን ላይ ባለኝ መረዳት ምን አልባትም በዚህ ወቅት ሰላም ለማስጠበቅ የሚሰራው ስራ ከመንግስት አካላትና ከፖለቲከኞች በላይ፣ ከህዝብ የሚጠበቅ መሆኑ ከቀደሙት ግዜያት ለየት የሚያደርገው ይመስለኛል። ሁሌም እንደሚባለው ምንም እንኳን ብዙውን ጊዜ ለችግራችን መነሻና መባባሻ የውጪ አካላት ጣልቃ ገብነት ያለበት ቢሆንም፤ አብዛኛው የሰላም እጦታችን መነሻውም መድረሻውም እኛው ኢትዮጵያውያን ነን። ምክንያቱ ደግሞ እኛ ጋር የተለየ በአለም ያልደረሰ ችግር ተፈጥሮ ሳይሆን ያለውን ሁኔታ ዘመኑ በደረሰበት የሰለጠነ እሳቤ በመነጋገር በመደማመጥ ለመፍታት የምናደርገው ተነሳሽነትና ርብርብ ዝቅተኛ መሆኑ ነው። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በጥቂት አካላት የተጀመሩ ነገሮችን በማህበራዊ ሚድያና በአካል ጭምር ቤንዚን አርከፍክፈን ያዘው በለው እያልን የምናባብሳቸውና ትልቅ ቀውስ የምንፈጥረው እኛው ነን።

በዚህ ረገድ ዘመኑ የደረሰበት ቴክኖሎጂና በየቀኑ እየተፈጠሩ ያሉ የመረጃ መለዋወጫ መሳሪያዎች ለእድገት፣ እንዲሁም ሰላምን ለማስጠበቅ በበጎ ለሚጠቀምባቸው የሚኖራቸው ፋይዳ አጠያየቂ አይደለም። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በአንዳንድ እኩይ አላማ ተሸካሚዎችና ገንዘብ ወዳድ ብልጣብልጦች ፤ እንዲሁም እኛ ራሳችን እንደ ዜጋ በሥርአትና በኃላፊነት ባለመጠቀማችን እያደረሱት ያለው ውድመት አስጊ ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል። ጥቂት የማንባል ሰዎች በማህበራዊ ሚድያ ማንም ለቃቅሞ ለገንዘብ ማግኛ የለጠፈውን እያየን ሌሎችን ከመተቸት ከመሳደብ አልፈን ራሳችንንም ጤና ስንነሳ እንሰነብታለን።

ትእግስት፤ ማጣራት፤ ማስተዋልና እኔስ ብሆን ብሎ ማሰብ እንደሀገር የራቁን ይመስለኛል። በየጎራችን... በየጎጣችን.... በየቡድናችን መሸገን መብታችን እንዲከበር የጠየቅነው ሁሉ እንዲመለስልን እንፈልጋለን። በተቃራኒው ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚያስደፍር መልኩ ሁላችንም ስለሌሎች መብት... ስለሌሎች ፍላጎት መሟላት... እንኳን ልንተባበር መስማት አንፈልግም። የኛ ባልናቸው ብልጣ ብልጦች የተነገረንን ሁሉ ደጋግመን ለራሳችን እየነገርን እኛ ብቻ ተበዳይ.... እኛ ብቻ ተገፊ.... እንደሆንን ይሰማናል። እናም ልዩነታችንን በትንሽ በትልቁ አስፍተን የገዛ ወገናችን ደስታ መነሻው የኛ ሀዘን ነው ብለን እናምንና የገዛ ሰላማችንን አጥተን የሌሎችንም ሰላም እስከማደፍረስ እንደርሳለን።

በዚህ መልኩ ጠብን ስንዘራ እንዳልቆየን ሁሉ፣ ትንሽ ግጭት ሲያጋጥም ደግሞ ያልዋልንበትን ፍሊጋ “ሰላም ሰላም” እያልን መዘመር እንጀምራለን። የሰላም ዋጋዋ ምን ያህል እንደሆነ ለመገንዘብ ግን አያት ቅድም አያቶቻችን የከፈሉትን መስዋእትነት ሳይሆን በራሳችን ዘመን ባለፉት አመታት ተከስቶ ያየነውን ብቻ ብናስተውል በበቃን ነበር። አንጻራዊ በሆነ መንገድ ዛሬ እያጣጣምነው ላለው ሰላም ብዙ እንደተከፈለ ባለቤቶቹ ነንና ምስክር አያሻንም። እንደ ሀገር የደረሰብን ቁሳዊ አካላዊና ስነልቦናዊ ቁስል ገና አልተፈወሰም።

በእርግጥ ባለፉት ተከታታይ ወራት እየሰማናቸው ያሉ የስምምነትና የአብሮነት ዜናዎች ምን አልባትም ሁላችንም ውስጥ የፈጠሩብን ደስታ እንዳለ የሚካድ ሀቅ አይደለም። ከዋና ዋና መገናኛ ብዙሀን እስከ ማህበራዊ ሚድያ የሚወራው ሁሉ የመጨባበጥ የመተቃቀፍ ከሆነ ውሎ አድሯል። መሽቶ በነጋ ቁጥር የሰቀቀን ዜና ለህዝባችን ለማድረስ የሚናፍቁት መርዶ ነጋሪ አንዳንድ የማህበራዊ ሚድያዎችና ነውጠኛ ፖለቲከኞችም ሳይወዱ በግዳቸው አፋቸውን ለመዝጋት ተገደዋል።

ይህም ሆኖ የሀገራችንና የህዝባችንን ሰላም በዘላቂነት ለማረጋገጥ የተሰሩትም ሆነ እየተሰሩ ያሉት ስራዎች የመጨረሻው ግብ ላይ ደርሰዋል ማለት አይደለም። ዝናብ ሲያባራ በአንድ ጊዜ እንደማይቆም ሁሉ፤ እዚህም እዛም ተስፋ ባልቆረጡ የጥፋት መልእክተኞች ጠብ ጠብ የሚሉ ነገሮች መኖራቸው አይቀርም። ለዚህ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ ምላሻችን በሶስት ነገሮች ላይ የተቃኘ ሊሆን ይገባል የሚል ምልከታ አለኝ። አንደኛውና ቀዳሚው ከሁሉም በላይ በህግ የበላይነት ማመንና ለህግ ተገዢ መሆን ነው። ይህንን ስል ለራሳችን ብቻ ሳይሆን በሀገራችን ጉዳይ ጥያቄም ሆነ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል በህግ ማእቀፍ ውስጥ ብቻ መንቀሳቀስ እንዳለበት በመቀበል ከዚህ ውጪ የሆኑ አካሄዶችን በተግባርም በንግግርም አምርረን ልንቃወም ይገባል።

ምክንያቱም ከላይ እንዳነሳሁት ዛሬም ድረስ ሀሳብን በሀይል ለማራመድ የሚንቀሳቀሱ አካላት መኖራቸውን እያየን በመሆኑ ነው። ሲሆን ሲሆን እነዚህ አካላት አንዳች ጎራ በመፍጠር ራሳቸውን የመጨረሻ መደበቂያቸው በማድረግ ሰላማችንን የሚነሱን በመሆኑ እዛው በእንጭጩ ከሀሳባቸው ጀምሮ ልንሞግታቸው ይገባል። ሀሳባችንን ተቀብለው ማንኛውንም አመለካከታቸውን በሰላም የማያራምዱ ከሆነ ደግሞ እንደ ማህበረሰብ በያለንበት የአጥፊዎች መሸሸጊያ ከመሆን መጠበቅ አለብን። ለእነሱ የመጣ እሳት ለእኛ ብርሃን ብቻ ሳይሆን ጥፋትም መሆኑ አይቀርም።

ሁለተኛው ጉዳይ፣ እንደ ህዝብ ከመሪዎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር የሚጠበቅብን ይሆናል። ህዝብ እንደ ህዝብ ከመሪዎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክረው እነሱ ትክክል ስለሰሩ ለመደገፍ በርቱ ቀጥሉ ለማለት ብቻ አይደለም። ይልቁንም የተሳሳቱ ነገሮችም ካሉ በቅርበት በመከታታል በወቅቱ ሰላምን በማያደፈርስ ጥፋት በማያስከትል መልክ እንዲስተካከሉ ለማድረግ እድል የሚሰጥ በመሆኑም ነው።

ሶስተኛውና መሰረታዊ ጉዳይ ባለፉት አመታት ውድቀታችንን መለያየታችንን በሚሹ አካላት የተሸረበብንን የእነሱና የእኛ አመለካከት መናድ ነው። ለሺ ዘመናት ስንኖር በውስጣችን ያለ ተፈጥሯዊ ልዩነት አንድነታችንን ህብረታችንን አፈራርሶት አያውቅም። የጣልያንን ወራሪ ከአንዴም ሁለቴ ገጥሞ የሀገሩን ነጻነት ያስጠበቀው ህዝብ አንድ ኢትዮጵያዊ በመባል ቢገለጽም የየራሱ ቋንቋ ባህልና ማንነት ያለው ኩሩ ህዝብ ነው። ዛሬም ያለው ይህው የየራሱ የሚያኮራ ማንነት ህዝብ ነው። ልዩነቶቻችን ደግሞ የውበታችን የኩራታችን ምንጭ ናቸው። እነዚህን ልዩነቶቻችንን አምነን ስንቀበልና የእኛ ስናደርጋቸው አንድነታችን የጸና ፤ ህብረታችን የተጠናከረ ይሆናል። ይሄ ያንተ አይደለም አልያም ይሄ አንተ አይደለህም እያሉ ሊበጣጥሱን የሚመጡትም መግቢያ ቀዳዳ አያገኙም። ይልቁንም ልዩነታችን የመለያያ ጉዳያችን አለመሆኑን ሲረዱ እነሱም እንደኛው ልዩነታችንን በውበትነት ለመቀበል ይገደዳሉ።

ባጠቃላይ እንደ ህዝብም እንደ ሀገርም የተጀመረው ሰላማችን እንዲጸና እንደ ዜጋ ከእኛ ብዙ እንደሚጠበቅ ልንገነዘብ ይገባል። ኢትዮጵያ የእኛ እንደመሆኗና ሰላሟ ሲናጋ እንደምንጎዳ ሁሉ ሰላሟን ለማስጠበቅም ቀዳሚ ተሳታፊዎች እኛው መሆን አለብን። በመሆኑም ትናንት በብዙዎች መስዋእትነት የተጠበቀልንን ሰላም ለማስቀጠል እኛም በየደረጃው ቢያንስ ለችግር መነሻና አባባሽ ባለመሆን ብዙ እየከፈልን ልንጠብቀው ይገባል እላለሁ።

> **እንደ ህዝብ ከመሪዎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር የሚጠበቅብን ይሆናል። ህዝብ እንደ ህዝብ ከመሪዎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክረው እነሱ ትክክል ስለሰሩ ለመደገፍ በርቱ ቀጥሉ ለማለት ብቻ አይደለም። ይልቁንም የተሳሳቱ ነገሮችም ካሉ በቅርበት በመከታተል በወቅቱ ሰላምን በማያደፈርስ ጥፋት በማያስከትል መልክ እንዲስተካከሉ ለማድረግ እድል የሚሰጥ በመሆኑም ነው**

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## የንግድ እንቅስቃሴውን የማነቃቃትና ሰላምን የማጽናት ዓላማ ያለው የትግራይ ተጓዥ ባዛር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ሁለት ዓመታትን ያስቆጠረው ጦርነት በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶችን አስከትሎ አልፏል። የኢትዮጵያ መንግሥት ፈቱንም ቢሆን ለሰላም ካለው ጽኑ አቋም በመነጨ ጦርነቱ የበለጠ ቀውስ ሳያስከትል ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲቋጭ በርካታ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል።

ጦርነቱ እንዲቆም አንዳንድ ምዕራባውያን አገሮች ሞካክረው ነበር፤ ይሁንና መንግስት ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ የሚል ጽኑ አቋም በመያዝ በአፍሪካውያን አወያይነት መንግስትና ሕወሓት ከሰላም ስምምነት ደርሰዋል።

በስምምነቱ መሰረትም በርካታ ተግባሮች ተከናውነዋል። በክልሉም ሆነ ክልሉ ከፌዴራል መንግስቱ ጋር የሚያደርጋቸው አገልግሎቶች በስፋት ተጀምረዋል። የአየር ትራንስፖርት፣ የቴሌኮም፣ የኤሌክትሪክ፣ የባንክ አገልግሎቶች በፍጥነት የተጀመሩ ሲሆን፣ በቅርቡ ደግሞ የየብስ የትራንስፖርት አገልግሎትና ሌሎችም አገልግሎቶች ተጀምረዋል፤ የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል።

ቀደም ሲል የተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች በትግራይ ጉብኝት ያደረጉ ሲሆን፣ በቅርቡም የክልል መስተዳድሮች በትግራይ ጉብኝት አርገዋል። መንግሥት በሰላም ስምምነቱ ማግስት በጦርነቱ የተጎዳውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ለማከም የሚያደርገውን ርብርብ ተያይዞታል።

ከእነዚህ ጥረቶች መካከል በጦርነቱ ምክንያት እጅግ የተጎዳው የትግራይ ክልል የንግድ እንቅስቃሴ አንዲያንሰራራ ማድረግ አንዱ ነው። ለዚህም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወደ ክልሉ ተጉዞ በንግዱ ዘርፍ ከተሰማሩ የተለያዩ አካላት ጋር ውይይቶችን በማድረግ የንግድ እንቅስቃሴው ወደ ቀድሞው የተነቃቃ እንቅስቃሴው እንዲመለስና ህብረተሰቡ ከንግድ ዘርፉ ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት ማግኘት እንዲችል አስቻይ ሁኔታዎችን የመፍጠር እንቅስቃሴውን በይፋ ጀምሯል።

ሚኒስቴሩ ደጋፊና ዋነኛ አስተባባሪ በመሆን ከትግራይ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር በመተባበር ‹‹የትግራይ የንግድ እንቅስቃሴ ለቀጠናዊ ሰላም›› በሚል የትግራይ ተጓዥ ባዛር ከሚያዝያ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚካሄድ ሰሞኑን የትግራይ ክልል ንግድ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አታኽልቲ ስዩም አስታውቀዋል።

አቶ አታኽልቲ እንዳሉት፤ የንግድ ባዛሩ በክልሉ የንግድ እንቅሰቃሴና አጠቃላይ ቀጠናዊ ትስስርን ለማጠናከር ዓላማ አድርጎ የተዘጋጀና በሁለት ዙር የሚካሄድ ይሆናል፤ የመጀመሪያው ዙር በመቀሌ፣ ውቅሮ አዲግራትና ማይጨው የሚደረግ ሲሆን፣ ለአንድ ወር የሚቆይ ነው። ሁለተኛው ዙር ደግሞ በዓብይ ዓዲ፣ ዓድዋ፣ አክሱምና ሽረ ይቀጥላል።

ባዛሩ ከመከፈቱ አስቀድሞ ሚያዝያ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ባለድርሻ አካላት በዋናነት ከፌዴራል የንግድና ፋይናንስ ተቋማት ጋር ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቦ የፓናል ውይይት ተደርጓል። ጥናታዊ ጽሑፉም የትግራይ የፋይናንስ ተቋማት ከየት እንደተነሱና አሁን ያሉበት ሁኔታ ተዳሷል። የትግራይ ክልል ቀጠናዊ የንግድ ትስስር አቅጣጫም ለውይይት ይቀርባል ነው ያሉት።

ባዛሩ በጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የነበረው ክልሉ ከክልሎችና ማእከል ጋር የሚያደርገው የንግድ ትስስር በጥሩ ሁኔታ መልሶ እንዲቀጥል ለማድረግና የኮንትሮባንድ ንግድን ለማስቆም እንዲሁም ነጋዴዎች ከአጋር ድርጅቶች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፣ በክልሉ ያጋጠመውን የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ለመፍታት ከባንኮች ጋር ለመስራት የሚያስችል ሁኔታ የሚፈጠርበት እንደሆነም ጠቁመዋል።

‹‹የባዛሩ ዋነኛ ዓላማ በእነዚህ አካባቢዎች መሰረታዊ የሆኑ የምግብ ሸቀጦችና ሌሎች ምርቶች እንደ ልብ ለማህበረሰቡ መድረስ እንዲችሉና ህዝቡ አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል ነው። በዚህም የተለያዩ የመንግሥት አካላትና የግሉ ባለሃብቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ወገን ለወገን በሚል መድረስ የሚችሉ ማንኛቸውንም አይነት ምርቶችና ሸቀጣ ሸቀጦችን በትግራይ ክልል ተደራሽ ለማድረግ በተለይም አምራቾች ጉልህ ሚና አላቸው››

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ስርዓትና ፈቃድ ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ተሻለ በልሁ እንዳሉት፤ ‹‹የትግራይ የንግድ እንቅስቃሴ ለቀጠናዊ ሰላም›› በሚል መሪ ሃሳብ መካሄድ የጀመረው የትግራይ ተጓዥ ባዛር እስከ ግንቦት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ለአንድ ወር ይካሄዳል። ባዛሩ በመንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ የመጣውን ሰላም ይበልጥ ለማጽናት ያስችላል። በክልሉ ተፋዞ የቆየውን የንግድ እንቅስቃሴ ያነቃቃል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ የትግራይ ተጓዥ ባዛር ዋነኛ ዓላማ በእነዚህ አካባቢዎች መሰረታዊ የሆኑ የምግብ ሸቀጦችና ሌሎች ምርቶች እንደ ልብ ለማህበረሰቡ መድረስ እንዲችሉና ህዝቡ አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል ነው። በዚህም የተለያዩ የመንግሥት አካላትና የግሉ ባለሃብቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ወገን ለወገን በሚል መድረስ የሚችሉ ማንኛውንም ምርቶችንና ሸቀጣ ሸቀጦችን በትግራይ ክልል ተደራሽ ለማድረግ በተለይም አምራቾች ጉልህ ሚና አላቸው።

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተካሄደው ጦርነት በሰላም ስምምነት መቋጨቱን ያስታወሱት አቶ ተሻለ፤ ሰላሙ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና የንግድ ሂደትን በአግባቡ መምራት መቻል የግድ እንደሆነም አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የትግራይ ክልል በአሁኑ ወቅት ጊዜያዊ አስተዳዳር አቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል። ይህን ተከትሎም ቢሮዎች ተቋቁመዋል። ከተቋቋሙ ቢሮዎች መካከል አንዱ የንግዱን ዘርፍ የሚመራው ኤጀንሲ ሲሆን፤ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከዚህ ኤጀንሲ ጋር በመቀሌ ተገኝቶ ውይይት አድርጓል። ባዛሩ የመጣው ሰላም ዘላቂነት እንዲኖረው የማድረግ እንዲሁም ተፋዞና ተቀዛቅዞ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ ማስቀጠል የሚያስችል ትልቅ አቅም ይኖረዋል።

በተለይም የተቀዛቀዘውን የንግድ እንቅስቃሴ ለማነቃቃት ከመሀል አገር ወይም ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች መሰረታዊ ሸቀጦች ወደ ትግራይ ክልል መዘዋወር እንደሚኖርባቸውም አስታውቀዋል። በተመሳሳይ ከትግራይ ክልል ወደ ሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች መሰረታዊ የሆኑ ሸቀጦችን ማንቀሳቀስም ይጠበቃል ሲሉ አቶ ተሻለ አስገንዝበዋል። በተለይ ንግድ በባህሪው ነጻ የሸቀጦች ዝውውርን እንደሚፈልግ ጠቅሰው፣ ለተግባራዊነቱም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ኃላፊነት እንዳለበት ገልጸዋል።

የክልሉን የንግድ እንቅስቃሴ ለማነቃቃት ወደ ትግራይ የሚደረገው ጉዞ በአማራ ክልል እና በአፋር በኩል እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ተሻለ፤ እነዚህን ሁለት አማራጭ መንገዶች በመጠቀም ከመሀል አገር ወደ ትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በሚደረግ እንቅስቃሴ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተገቢውን ማስረጃ ለመስጠት እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

ያም ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶች ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ሸቀጥ በአገር ውስጥ በነጻነት ይንቀሳቀሳል ሲሉ አቶ ተሻለ ገልጸዋል። ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች ከሆኑ ለኤክስፖርት ንግድ የተዘጋጀ የአሰራር ስርዓት እንዳለም አስታውቀዋል፤ ይህም ስርዓቱን ተከትሎ እንደሚፈጸም ተናግረዋል። ከዚህ ውጭ የሆኑ ለአብነትም የምግብ ዘይት፣ ስኳርና ሌሎች መሰረታዊ ሸቀጦችን በየትኛውም የአገሪቱ ጫፍ በነጻነት ማንቀሳቀስ እንደሚቻል አስረድተዋል።

ምርቶቹ በአካባቢው ተደራሽ ሆነው ማህበረሰቡ የሚፈልጋቸውን የምግብ ሸቀጦችና ሌሎችንም አገልግሎቶች ማግኘት እንዲችል ብዙ ሥራ ይጠበቃል ሲሉም አመልክተው፣ ይህም የተነቃቃ ንግድ ለማምጣት እንደሚያስችል ነው ያስታወቁት። ንግዱ ሲነቃቃ ሰላሙን በበለጠ መንገድ ማጠናከር እንደሚችልም ጠቅሰው፣ የተጠናከረ ሰላም ደግሞ ትግራይን ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት እንደሚያስችል ተናግረዋል። ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን በማጠናከር ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ነው አቶ ተሻለ ያብራሩት።

የትግራይ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተወካይ አቶ ካህሳይ ላዕከ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የትግራይ ተጓዥ ባዛር ክልሉ ያጋጠመውን የንግድ እንቅስቃሴ ችግር በጊዜያዊነትና በቋሚነት መፍታት ያስችላል።

የክልሉ የንግድ እንቅስቃሴ ውስብስብና ከፍተኛ ችግር የገጠመው መሆኑን አቶ ካህሳይ ጠቅሰው፣ ችግሩን በዘላቂነት መፍታት እንዲቻል የባዘር ዝግጅቱ አስፈላጊና ወሳኝ ነው ይላሉ። ከዝግጅቱ አንዱ በሆነው በፓናል ውይይት የቢዝነስና የፋይንንስ ተቋማት እንደሚሳተፉ አስታውቀው፣ በውይይቱም ክልሉ ከገጠመው ችግር ተላቆ ወደ ቀድሞ ሰላማዊ የንግድ እንቅስቃሴው መመለስ የሚችልበትን መንገድ ለማምጣት እንደሚጠቅም አስረድተዋል።

እንደ አቶ ካህሳይ ገለጻ፤ በክልሉ ከፍተኛ የሸቀጦች እጥረት ይታያል። ችግሩን በጊዜያዊነት ለመፍታት አምራቾች፣ አስመጪዎችና አከፋፋዮች ከፍተኛ ሚና አላቸው። አምራቾች፣ አስመጪዎችና አከፋፋዮች በባዛር መልክ ወደ ክልሉ ተጉዘው የህብረተሰቡን ችግር በአቅርቦት፣ በጥራትና በዋጋም ጭምር በመፍታት ማህበረሰቡን ማገዝና መደገፍ ይችላሉ። በተመሳሳይ ራሳቸውም ሸቀጦችንና አገልግሎታቸውን በመሸጥ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። በመሆኑም ሁሉም አምራቾች፣ አስመጪዎችና ገበያ የሚፈልጉ በሙሉ በባዛሩ መሳተፍ ይችላሉ፤ ለዚህም እንደ ክልል ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጓል።

የትግራይ ተጓዥ ባዛር ባለፉት ሶስት ዓመታት ተዳክሞ የቆየውን የትግራይ ክልል የንግድ እንቅስቃሴ ማነቃቃት እንደሚያስችልና የንግድ እንቅስቃሴውን ወደ ቦታው የመመለስ አቅም እንዳለው አቶ ካህሳይ አስታውቀዋል። ለዚህም ሰላም መምጣቱ ዋናው ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ ነው ያስታወቁት። ለተግባራዊነቱም የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የክልሉ የንግድና የቢዝነስ እንቅስቃሴ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ጠቅሰው፣ ለዚህም ድጋፍ እንደሚያደርግ እምነቱ እንዳላቸው ገልጸዋል።

አቶ ካህሳይ የንግዱ ዘርፍ በፓናል ውይይትና በባዛር መልክ የሚያደርገው የንግድ እንቅስቃሴ ሁለት ተልዕኮ እንዳለው አስታውቀዋል፤ አንደኛው በክልሉ ሰላማዊ የንግድ እንቅስቃሴ መካሄድ መጀመሩን ለማሳየት፣ ሁለተኛው ደግሞ የክልሉ ህዝብ የገጠመውን የሸቀጦችና የመሳሰሉት አቅርቦቶች ጉድለት ቀረብ ብሎ በመረዳት ክፍተቱን መሙላት መሆኑን አመልክተዋል። በክልሉ ከተሞች የተፈጠረውን ጉድለት ለመሙላትና የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ጥረት እንደሚደረግም አስረድተዋል።

የትግራይ ተጓዥ ባዛር፤ በዋናነት የትርፋማነት አጀንዳ ሳይሆን ለማህበረሰቡ አግልግሎት መስጠትና እሴት መጨመር እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ካህሳይ፤ የንግድ ባዛሩ በተለይም ሰላምን የማጽናትና የእርስ በእርስ ግንኙነትን ማጠናከር አንዱና ዋነኛው ተልዕኮው እንደሆነ ነው የተናገሩት።

ሌላው በአካባቢው የተፈጠረውን የአቅርቦት ክፍተት የመሸፈን እንዲሁም አገልግሎት መስጠትን ዋና ዓላማው አድርጎ በሚካሄደው የትግራይ ተጓዥ ባዛር ላይ የሸቀጣ ሸቀጦች ዝውውር ባልተገደበ ሁኔታ እንዲፈጸም ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግም እሳቸውም አመላክተዋል።

በጦርነቱ ክፉኛ የተጎዳውን የንግድ እንቅስቃሴ ለማነቃቀት አሁን የተፈጠረው ሰላም እጅግ ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም ለአንድ ወር የሚካሄደው የትግራይ ተጓዥ ባዛር የመጣውን ሰላም ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ እንዲሁም የህዝቦችን የእርስ በእርስ ግንኙነት በማጠናከር ጤናማ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲፈጠር እንደሚያስችል ታምኖበታል።

በባዛሩ በተለይም የንግዱ ዘርፍ በሁሉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ በክልሉ የተፈጠረውን የአቅርቦት እጥረት በዋጋና በጥራት በመሙላት የክልሉን የንግድ እንቅስቃሴ ወደ ቀድሞ ቦታው ለመመለስ የሚጠበቅበትን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ዛሬ የሚለምኑ ሕጻናት ነገ ምን ይሆናሉ?

**ዋለልኝ አየለ**

በምንም አይነት መንገድ ይሁን በአገራችን ሰላም መስፈን አለበት፤ አለበት ብቻ ሳይሆን በጣም የግድ ነው። አለበለዚያ የትውልድ ክፍተት ይፈጠራል። አሁን የምናየው ሁኔታ ከዚህ በላይ ከቀጠለ የማይተዋወቅ ትውልድ ይፈጠራል፤ ከአንድ ትውልድ በኋላ የሚኖረው ማህበረሰብ ጨካኝና የሚበላላ ሊሆን ይችላል።

አዲስ አበባ ውስጥ በተንቀሳቀሳችሁባቸው አካባቢዎች ሁሉ ልብ ብላችኋል? በትራንስፖርት መሰለፊያ ቦታዎች፣ በምግብ ቤቶች በር ላይ እና በአጠቃላይ በየጎዳናዎች ዳር ላይ የሚለምኑ ሕጻናትና እናቶችን ታዝባችሁ ታውቃላችሁ? መታዘብ ሲባል ‹‹ለምን ለመኑ?›› በሚል አይደለም፤ በምን ምክንያት ለልመና ተዳረጉ? የሚለውን ነው።

አሁን አሁን በጣም ከመብዛቱና ከመለመዱ የተነሳ መደበኛ ሕይወት አድርገነዋል። ሁለትና ሦስት ሕጻናት ልጆች ይዛ የምትለምን እናት አይቶ የሚረበሽ ብዙም አይኖርም፤ ምክንያቱም ተለመደ፤ መደበኛ ሕይወት ሆነ። መንገድ ዳር ዝናብና ፀሐይ የሚፈራረቅባቸውን ሕጻናት ማየት እያስደነቀ አይደለም።

ከምንም በላይ የከፋ የሆነው ግን የታዳጊ ልጆች በየምግብ ቤቱ በር ላይ እና በየመስመሩ መብዛታቸው ነው። በራሳቸው የሚለምኑት እንዳሉ ሆነው ከወላጆቻቸው ጋር የሚለምኑ ትንንሽ ሕጻናት ደግሞ አሉ። ምግብ ቤቶች ውስጥ ሲገቡ የአስተናጋጆችና የባለቤቶች ቁጣ ይገላምጣቸዋል። ባለቤቶችም ነጋዴ ናቸውና አይፈረድባቸውም፤ ደንበኛው(ተጠቃሚው) ምቾት ስለማይሰጠው ነው በቁጣ ‹‹ውጡ!›› የሚሏቸው።

በዚህ ሁሉ ትዕይንት ውስጥ አንዳንዱ ምንም ሳይመስለው ምግቡን ቢበላም አንዳንዱ ደግሞ ሰውነታቸው የጠወለገ ሕጻናትን እያየ መብላት ውስጡ ይላወሳል። ሕጻናት አይናቸው ቅርጭም ቅርጭም እያለ መብላት ያሳቅቃል።

ሌላው ደግሞ በየመስመሩ ዳር ሕጻናት ልጆችን ይዘው የሚለምኑት ናቸው። ቀደም ሲል እንዳልኩት ከመለመዱ የተነሳ መደበኛ ሕይወት አድርገነዋል። ለዚህም ነው ሕጻናቱ አላፊ አግዳሚውን ልብሱን ይዘው ‹‹ጋሼ ዳቦ ግዛልኝ!›› ሲሉ አንዳንድ ሰዎች ‹‹ልቀቀኝ!›› ወይም ‹‹ልቀቂኝ!›› በማለት እጃቸውን መንጭቀው የሚቆጧቸው። እነዚህ ሰዎች ምናልባትም ከሌላው ሰው በተለየ ሰብዓዊነት የሌላቸው ሞራለ ቢስ ሆነው አይደለም፤ መደበኛ ሕይወት ስለተደረገ ነው።

በሌላ በኩል፤ ችግራቸውን አያውቁላቸውም። የችግሩ ገፈት ቀማሽ ዘመድ አዝማድ የሌላቸው ሰዎች የሚያስቡት ሕጻናቱ የሚለምኑት በወላጆች ትዕዛዝ ብቻ ነው ብለው ነው። ወላጆች ደግሞ የሚያዟቸው ሥራ መሥራት ሰንፈው ለልመና ሱስ ብቻ ነው ተብሎ ይነገራል። የሚለምኑ ሰዎችን ‹‹ሰርተህ አትበላም?›› የሚል የተግሳጽ ምክር እንሰማለን፤ እየተባባሰ ሲሄድ እንጂ ችግሩን ሲቀርፍ ግን አልታየም።

ልመና እጅግ አፀያፊ ነገር ነው። የሚለምኑት ሰዎችም አፀያፊነቱን ያውቃሉ። ምናልባትም ከአቅም በላይ ሆኖባቸው ይሆናል። ይህ ማለት ግን በስንፍና ብቻ የሚለምኑ የሉም ማለት አይደለም። እያወራን ያለነው ስለጠቅላላው የልመና ምክንያት ስለሆነ ነው።

ከልመና ምክንያቶች አንዱና ዋናው የሰላም እጦት ነው። ምንም ሰፊ ጥናትና ምርምር ሳያስፈልገው ማንም ሰው ማረጋገጥ የሚችለው ነው። አጠገባችሁ ያለች እናት ወይም ሕጻን ልጅ ከየት እንደመጡ እና ለምን እንደሚለምኑ ብትጠይቋቸው ከመጡበት አካባቢ ችግር ስለነበር ነው። ይህ ሲባል ወደ ብዙዎቻችን አዕምሮ የሚመጣው ምናልባትም የሰሜኑ ጦርነት ነው። ዳሩ ግን ልብ ያልተባሉ ብዙ የሰፈር ሽፍታዎች ሁሉ ማፈናቀል ጀምረዋል። ሰው እያገቱ ብር ያስልካሉ፤ በዚህ ምክንያት መገዳደል ይመጣል፤ በዚሁ ምክንያት ሰዎች ይሰደዳሉ። ይህ የሚሆነው ከህጋዊ ውጭ ባሉ የመንደር ታጣቂዎች ነው። ለምን ዓላማ ሰው እንደሚገድሉ በማያውቁ ሽፍታዎች ነው።

ሌላው የልመና ምክንያት ከማህበራዊ ሕይወታችን የሚቀዳ ነው። ማህበራዊ ሕይወታችን ብዙ አኩሪ እሴቶች እንዳሉት ሁሉ መቀረፍ ያለባቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችም አሉበት። ለምሳሌ፤ ያለዕድሜ ጋብቻ እና ያለአቻ ጋብቻ የብዙዎችን ሕይወት አተረማምሰዋል። አንዲት ሴት ልጅ ያለዕድሜዋ ስትዳር ከአካላዊ ጉዳት ጀምሮ እስከ አዕምሯዊ ህመም ትዳረጋለች። የዚች ልጅ ዕጣ ፋንታ የሚሆነው ጎዳና መውጣትና መለመን ነው።

በየመንገዱ ለልመና ከተዳረጉ እናቶች አብዛኞቹ ምናልባትም ተገደው ተደፍረው የወለዱ ናቸው። ያለአቻቸው በግዴታ ተድረው ግፍ ሲበዛባቸው ልመና ይሻላል ብለው ወደ አዲስ አበባ የሚሄዱ ናቸው። የአካባቢያቸው ሕይወት ከልመና የከፋ ሆኖባቸው ሸሽተ የመጡ ናቸው።

ከምንም በላይ የከፋ የሆነው ግን የሰላሙ ጉዳይ ነው። እኔ በማውቀው አካባቢ እንኳን ብዙ ሰዎች የተሰደዱት በመንደር ሽፍታዎች ነው። የመንደር ሽፍታ የቆመለት ዓላማ የለውም። ሰው ገድሎ ወይም ንብረት ዘርፎ ወይም አስገድዶ ደፍሮ ከሕግ ለማምለጥ ጫካ የገባ ነው። በእነዚህ ሽፍታዎች ምክንያት ብዙ ዜጎች እየተፈናቀሉ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ለዝናብና ፀሐይ ተዳርገዋል። ወደ አዲስ አበባ መሸሽ ያልቻሉት ወይም የመጣው ይምጣ ብለው የተቀመጡት ከመንግሥት የሚፈልጉት ሰላምን እንዲያስከብርላቸው ነው።

ይህን አስከፊ የልመና መስፋፋት የምናስቀረው በመጀመሪያ ሰላም ሲሰፍን ነው። ሰላም የሚሰፍነው ደግሞ ሁላችንም ለሰላም ስንሰራ ነው። አንድ አካል ብቻ ሰላም እንዲያመጣ ከጠበቅን አይመጣም። ከመንግሥት በላይ ሰላምን ማምጣት የሚችለው ሕዝብ ነው። አንድ ጥሩ ምሳሌ ልጥቀስ!

የመንግሥት የፀጥታ አካላት ወደ ሕብረተሰቡ ገብተው ሕብረተሰቡን ወንጀለኞችን ጠቁሙ ሲባል አይጠቁሙም። እንዲያውም ወንጀለኛውን ለመደበቅ የሚተባበሩ ሁሉ አሉ። ይህ የሚሆነው አንዳንዶቹ በአድርባይነት፣ አንዳንዶቹ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ስለማይወስድ ለምን ከሽፍታው ጋር ቂም ውስጥ እገባለሁ በሚል በተስፋ መቁረጥ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ምናልባትም ከሽፍታው የሚያገኙት ጥቅም ስለሚኖር ነው። ይህ ሁሉ ጣጣ ስለሚኖር ሰላም ፈላጊዎች መንግሥትን መተባበር አለባቸው።

አለበለዚያ የትውልድ ክፍተት ይፈጠራል፤ ልመናም አገራችንን እያቃወሰ ነው። እነዚህ በየምግብ ቤቱ በር ላይ ያሉ ልጆች ትምህርት እየተማሩ አይደለም፤ ቀጣይ ሕይወታቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ለማንም ቀላል ነው። ከዛሬ ምናምን ዓመታት በኋላ እነዚህ ልጆች ያልተማረ ዜጋ ነው የሚሆኑት። ከዛሬ ምናምን ዓመታት በኋላ ዓለም የት እንደምትደርስ ማሰብ ቀላል ነው። መጻፍና ማንበብ የማይችል ማህበረሰብ የሚኖርባት ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ ልትሆን ትችላለች። ይህንን እያሰብን ነው መሥራት ያለብን።

በየአካባቢው ሰላም ከሰፈነ በኋላ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ይቻላል፤ ትምህርት ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ይከፈታሉ። መሰረተ ልማቶች ሲሰሩ የዘመኑ ውጤት የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ ይሆናሉ። ያኔ የሰዎች አመለካከትም ዘመናዊ ይሆናል። ስለዚህ መንግሥትም ሕዝብም ለሰላም ይስራ፤ ልመናን እናስቀር!

# ዓለም አቀፍ

## የሕንድ ግዛት ጠጪና ከልክ በላይ ውፍረት ያላቸውን ፖሊሶች ከሥራ ልታሰናብት ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የሕንድ አንድ ግዛት በሆነችው አሳም የአልኮል መጠጥ ሱሰኛ የሆኑ እንዲሁም ከልክ በላይ የወፈሩ የፖሊስ አባላት ከሥራቸው ሊሰናበቱ ነው።

የግዛቲቱ ባለሥልጣናት እንዳሉት፤ በተለይ የአልኮል መጠጥ ችግር አለባቸው የተባሉ 300 የሚደርሱ የፖሊስ መኮንኖች በፈቃዳቸው ሥራቸውን እንዲለቁ እየተጠየቁ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

የግዛቲቱ ዋና አስተዳዳሪ ሂማንታ ቢስዋ ሳርማ እንደተናገሩት፤ በተጠቀሱት የፖሊስ ሠራዊቱ አባላት ዘንድ ያለው የአልኮል ሱሰኝነት ችግር ጤናቸው ላይ እክል እየፈጠረ በመሆኑ ከዕድሜያቸው ቀድመው ጡረታ እንዲወጡ ተጠይቀዋል።

አስተዳዳሪው ጨምረውም ከአልኮል መጠጥ ሱሰኞች የፖሊስ አባላት በተጨማሪ፣ ከልክ በላይ ውፍረት ያላቸው ፖሊሶች እንዲሁም፣ የሙስና ክስ ያለባቸው የፖሊስ መኮንኖችም በፈቃዳቸው ከሥራቸው እንዲሰናበቱ ሊጠየቁ ይገባል ብለዋል።

የግዛቲቱ አስተዳደር በተለያዩ ምክንያቶች በተገቢው ሁኔታ የፖሊስ ሥራቸውን ለማከናወን የማይችሉ አባላትን የማሰናበት ውሳኔ ላይ የደረሰው፣ ዋና አስተዳዳሪው “ዋጋ የላቸውም” ያሏቸውን የፖሊስ አባላትን የሚያስወግድ እርምጃ እንደሚወስዱ ካሳወቁ በኋላ ነው።

በመጠጥ ሱስ፣ በከፍተኛ ውፍረት እና በሙስና የሚታወቁ አባላትን ከፖሊስ ሠራዊቱ ከተሰናበቱ በኋላ፣ የግዛቲቱ የፖሊስ አዛዦች የአባሎቻቸውን ሥነ ምግባር ከመከታተል ባሻገር፣ ሸንቃጣ እና ለሥራው ብቁ መሆናቸውን መቆጣጠር እንዳለባቸው አስተዳዳሪው አዘዋል።

የአልኮል ሱሰኝነት ከልክ ያለፈ ውፍረትን ጨምሮ ለተለያዩ ጤና ችግሮች እና ለሙስና በር እንደሚከፍት የሚታመን ሲሆን፣ የግዛቲቱ አስተዳደርም እነዚህን ችግሮች ትኩረት ሰጥቶ ለማስተካከል እየሰራ ነው።

# ስፖርት



# ፈተና ያልበገራቸው የኢትዮጵያ ወጣት አትሌቶች በድል አሸብርቀዋል

**ብርሃን ፈይሳ**

በአስደሳች ድሎች፣ አወዛጋቢ ውጤቶች እንዲሁም ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ያለፈው የአፍሪካ ወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ዛሬ ይጠናቀቃል። በዛምቢያ ናዶላ ከተማ አዘጋጅነት ይህ ቻምፒዮና ከ18 እና 20 ዓመት በታች የሚካፈሉበት ውድድር ሲሆን፤ በጥምረት መካሄድ ከጀመረ ዘንድሮ ሁለተኛ ጊዜው ነው። በየፊናቸው ይካሄዱ የነበሩት እነዚህ ውድድሮች ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮናው ዘንድሮ ለ15ኛ ጊዜ፣ ከ18 ዓመት በታች ቻምፒዮናው ደግሞ ለ4ኛ ጊዜም ነው የተከናወነው።

የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን የሚመራው በዚህ ውድድር ላይ 50 ሃገራት አትሌቶቻቸውን ከ18 ዓመት በታች በ40 እንዲሁም ከ20 ዓመት በታች በ44 የውድድር ዓይነቶች አሳትፈዋል። ከእነዚህ መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ስትሆን ብሄራዊ ቡድኗ እስከ ትናንት ቀትር ድረስ 6 የወርቅ፣ 4 የብር እና 3 የነሃስ በጥቅሉ 13ሜዳሊያዎች ተመዝግበዋል። አስደሳች ድሎችና አወዛጋቢ ውጤቶች በተመዘገቡበት ቻምፒዮና ፈታኝ ሁኔታዎችን ለማሳለፍ የተገደደው ወጣት ቡድኑ ለዚህ መድረሱም እጅግ የሚያስመሰግነው ሆኗል።

ሃገራቸውን ወክለው በውድድሩ የተካፈሉት የቡድኑ አባላት ከ30 ያላነሱ አትሌቶች ሲሆኑ፤ በሁለቱም ጾታ እና የዕድሜ እርከኖች ከ800 ሜትር ጀምሮ እስከ 10 ሺህ ሜትር ድረስ ባሉ የውድድር ርቀቶች ተካፋይ ነበሩ። በዚህም ከ18 ዓመት በታች በጥቅሉ 3 ሜዳሊያዎች ሲመዘገቡ፤ ከ20 ዓመት በታች ደግሞ 10 ሜዳሊያዎች ተመዝግበዋል። በመጀመሪያው ዕለት ከተካሄዱ ውድድሮች ኢትዮጵያዊያን የተካፈሉበት የፍጻሜ ውድድር ከ20 ዓመት በታች 3ሺ ሜትር



**በ3ሺ ሜትር ሴቶች ከ20 ዓመት በታች ውድድር ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ያለውን ደረጃ በመያዝ አጠናቀዋል፤**

ሴቶች ሩጫ ከወርቅ እስከ ነሃስ ያሉትን ሜዳሊያዎች ጠራርጎ በመውሰድ ነበር ውደድሩ የተጀመረው። የድሉ ባለቤቶችም አትሌት አስማረች አንለይ፣ የኔዋ ንብረት እና አይናዲስ መብራቱ ናቸው።

በውድድሩ የሁለተኛ ቀን ውሎም ከ20 ዓመት በታች የሴቶች 1ሺ500ሜትር በተመሳሳይ ውብርስት አስቻለ፣ ሳምራዊት ሙሉጌታ እና ምጥን እውነቱ ተከታትለው በመግባት ከአንድ እስከ ሶስት በመውጣት ድሉን አስመዝግበዋል። በወንዶች በኩል ደግሞ አሸናፊ ኢማና ሁለተኛ በመሆን ሲገባ፤ ሁለት ዲፕሎማዎች ተገኝተዋል።

ከ18 ዓመት በታች በ3ሺ ሜትር ርቀት ማርታ ዓለማየሁ የብር ሜዳሊያ ባለቤት ስትሆን፤ በ2ሺ ሜትር መሰናክል ወንዶች ደግሞ ኦብሳ ፈይሳ የነሃስ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆኗል።

በሶስተኛው ቀን በተካሄዱ የፍጻሜ ውድድሮችም ከ18ዓመት በታች 3ሺ ሜትር መሰናክል ሰውመሆን አንተነህ የወርቅ ባለቤት ሊሆን ችሏል። ከ20 ዓመት በታች የወንዶች 10ሺ ሜትር እርምጃ ውድድርም የወርቅ ሜዳሊያው በምስጋና ዋቁማ ተመዝግቧል። ከ20 ዓመት በታች ሴቶች 3ሺ ሜትር መሰናክል ደግሞ አለምናት ዋለ እና ፍሬህይወት ገሰሰ ተከታትለው በመግባት የወርቅና የነሃስ ሜዳሊያውን ወስደዋል። ይሁንና በዚህ ርቀት የተገኘው ሜዳሊያ የውዝግብ መንስኤ ሊሆን መቻሉን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በድረገጹ አስነብቧል።

ይኸውም ከ20 ዓመት በታች የ3ሺ ሜትር መሰናክል ሴቶች ውድድር ለኢትዮጵያ የተመዘገበው የወርቅና የብር መሜዳሊያ አሸናፊ የሆኑ አትሌቶች እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ሆኖ የተወዳደሩት ግን ከ20 ዓመት በታች ውድድር ላይ በመሆኑ ነው። የተነሳው የተገቢነት ጥያቄም «ከእድሜያቸው በላይ በሆነ ውድድር ገብተው መወዳደር አይችሉም» የሚል ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በበኩሉ «ከታችኛው የእዕሜ ደረጃ ወደ ላይኛው ዕድሜ ጣራ መወዳደርን የዓለም አትሌቲክስ ስለሚፈቅድ መብታችን ነው» የሚል አቋም ይዟል። በዚህም ምክንያት ዘገባው እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ውጤቱ በሜዳሊያ ሰንጠረዡ ውስጥ አለመካተቱን አዲስ ዘመን አረጋግጧል።

ብሄራዊ ቡድኑ ከቀናት በፊት በአትሌቶቾ ስነልቦና አሉታዊ ስሜት ሊያሳድር የሚችል አስቸጋሪ ሁኔታም ገጥሞት ነበር። ይኸውም ከውድድሩ የመክፈቻ ስነስርዓት በኋላ መኙታ ማጣቱን ተከትሎ ውድድሩ ከሚካሄድበት ከተማ እስከ 65 ኪሎ ሜትር ለመጓዝ ተገዷል። ሆኖም መኙታ ባለማግኘቱና አግባብ ያልሆነ ምላሽ በማግኘቱ የቡድኑ አባላት ለሊቱን በመሬት ላይ እንዲሁም በወንበር ላይ ተኝተው ለማሳለፍ ተገደዋል። ሆኖም አባላቱ ጽናታቸው በሚያስመሰክር መልኩ በነገታው በተካሄደው ውድድር ተከታትለው በመግባት ከወርቅ እስከ ነሃስ ያለውን ሜዳሊያ መውሰዱ በርካቶችን አስደንቋል። ዛሬ በሚካሄዱ የፍጻሜ ውድድሮችም ቻምፒዮናው የሚጠቃለል ይሆናል።

# ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የሙያ ደህንነት አጠባበቅና የደንበኛ አያያዝ

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

በየአመቱ በፈረንጆች አፕሪል 28 በሀገራችን አቆጣጠር ደግሞ ሚያዚያ 20 የሙያ ደህንነት ጤንነት ቀን በአለም አቀፍ ደረጃ ይከበራል። ይህ ቀን "ድህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የስራ አካባቢ መሰረታዊ መርህ እና የስራ ላይ መብት ነው።" በሚል መሪ ቃል በመላው አለም በተለያዩ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ተከብሮ የሚውል ሲሆን የሙያ ደህንነት ጤንነት ቀን መሰረታዊ አላማ በስራ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶችን በመከላከልና በቀነስ ረገድ አሳታፊ የተቀናጀና ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ለሁሉም የአሰሪና ሰራተኛ ማህበራት ወኪሎች፣ ለመንግስት አስፈፃሚ አካላት እና አህባብነት ላላቸው ሌሎች አጋሮች የሴፍቲ ባህልን ይበልጥ የማስረፅና የመገንባት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲተገበር ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ላይ ያተኮረ ነው።

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትም ይህንን ቀን ሚያዚያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ለባስ ካፒቴኖች የሙያ ደህንነት አጠባበቅና የደንበኛ አያያዝ ላይ ያተኮረ ስልጠና በመስጠት አክብሮታል። የሙያ ደህንነት እና ጤንነትን አስመክቶ ለባስ ካፒቴኖች ስልጠና የሰጡት በስራና ክህሎት ሚኒስቴር የሙያ ደህንነትና ጤንነት ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት አቶ አብነት ፍቃዱ ናቸው። በየአመቱ በአለማችን ላይ የሚከሰቱ የስራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶችን ሁኔታ በምንመለከትበት ጊዜ የአለም ስራ ድርጅት እ.ኤ.አ በ2019 ባወጣው ይፋዊ ሪፖርት መሰረት፤ በምርታማ ስራ ላይ ተሰማርቶ በነበረው ሁለት ነጥብ 69 ቢሊዮን የሰራተኛ ህዝብ ላይ 331 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የስራ ላይ አደጋዎች መከሰታቸውን የሚያመላክት ሲሆን ከእነዚህ መካከል 181 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሚገመቱት ስራ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ህመሞች ሳቢያ የጤና ጉዳቶች ሪፖርት መደረጋቸውን፤ በተከሰቱ የስራ ላይ



አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች ሳቢያ ሁለት ነጥብ 34 ሚሊዮን የሚገመቱ ሰራተኞች ህይወታቸውን ያጡ መሆናቸውን የሚያሳይ መሆኑን ገልፀዋል። በዚህ ሳቢያ በጉዳቱ ሳቢያ ሀገራት ከብሄራዊ አጠቃላይ ገቢያቸው(GDP) ከአራት እስከ አምስት በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ያጡ መሆኑንና ለስራ ላይ አደጋዎችና ለጉዳቶች መከሰት በዋነኝነት ከተለዩ ምክንያቶች መካከል ደረጃቸውን ያልጠበቁ የስራ ሁኔታዎች፣ ደካማ የህግና የቁጥጥር አሰራር እንዲሁም የሴፍቲ ግንዛቤ እና ባህል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ተጠቃሽ እንደሆን አመላክተዋል።

እንደ አቶ አብነት ገለፃ፤ የሙያ ድህንንት ጤንነት ባህል፤ በሰራተኞች፣ በተቋማት፣ በስራ አመራር አካላት እና በማህበራት ዘንድ ሊፈጠር የሚገባ የጥንቃቄና የደህንነት አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ዝንባሌ የሚገለፅ፣ በውይይትና በምክክር ሂደት የሚጎለብት፣ በየጊዜው እየተለወጠ እያደገና እየተሻሻለ የሚሄድ፣ በመረጃና በተጨባጭ ምክንያታዊነት የሚብራራ፣ ለአሰራር ስርዓትና ለመርሃ ግብር መሰናዶ በግብዓትነት የሚውል ሀብት ከመሆኑ ባሻገር በህግ መሰረት የተደነገጉ መብትና ግዴታዎችን ያማከለ ሊሆን ይገባዋል።

የመንግስት አስፈፃሚ አካላት፤ የሚመለከታቸውን የመንግስት መዋቅሮች በየደረጃው ያሉ የአሰሪና ሰራተኛ ማህበራትን የፍትህ አካላትና መላው ህብረተሰብ በማስተባበር የሴፍቲ ትምህርት እና ግንዛቤ የማሳደግ ስራ እንዲስፋፋ ማድረግ ይኖርባቸዋል የሚሉት ባለሙያው፤ ለሀገሪቱ ፈጣን እድገት አጋዥ የሆኑ ከሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እና ከተስማሚ የቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር የተገናዘቡና በጥናት የተደገፉ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም የስራ ደረጃዎች በጥናት ላይ ተመስርቶና ከአሰሪዎችና ከሰራተኛ ማህበራት ወኪሎች ጋር በመመካከር ማውጣት ወይም መከለስ እና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። የሴፍቲ ግንዛቤን በማሳደግ ረገድ ደረጃቸውን የጠበቁ የትምህርት ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት ውጤታማነታቸውን መፈተሽና በተለያዩ የስራ ቋንቋዎች በመተርጎም ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በፐበሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የአሽከርካሪዎች ንድፈ ሃሳብ አሰልጣኝ የሆኑት አቶ ያሬድ መስፍን፤ ለባስ ካፒቴኖች በሰጡት የደንበኛ አያያዝ ስልጠና፤ የባስ ካፒቴኖች ሁሌም የስራ ሰዓታቸውን አክብረው በስራ ገበታቸው ላይ በመገኘት አገልግሎቱ ባስቀመጠው የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ፐብሊክ ሰርቫንቱን በአግባቡ ማስተናገድ እንዳለባቸው ገልፀው፤ ባስ ካፒቴኖች ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት የተሽከርካሪዎቻቸውን ደህንነት ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ከዚህ በተጨማሪ አገልግሎቱን በሚሰጡበት ወቅት አገልግሎት ተጠቃሚው ሊያሟላ የሚገባቸውን መረጃዎች ማሟላቱን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ገልፀው ይህም አንድ የፐብሊክ ሰርቪስ ተጠቃሚ የሚሰራበትን መስሪያ ቤት መታወቂያና የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስችለውን የአገልግሎቱን መታወቂያ መያዙን ማረጋገጥ መሆኑን አብራርተዋል።

ፌርማታዎች ላይ በአግባቡ በማቆም ደንበኛን በሚፈልገው ፌርማታ ላይ ማውረድ አስፈላጊ በመሆኑን ያስረዱት አሰልጣኙ፤ የባሶቹን በሮች በሚከፈቱበትና በሚዘጉበት ወቅት ጉዳት እንዳይደርስና ተጠያቂነትን እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል።

እንደ አቶ ያሬድ ገለፃ፤ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በስራ መግቢያ መውጫ ሰዓት ለፐብሊክ ሰርቫንቱ ከሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት በተጨማሪ ከስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ ለቀሪው የማህበረሰብ ክፍል የትራናስፖርት አገልግሎት በመስጠት ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ ሁሉም የባስ ካፒቴኖች በአግባቡ በፌርማታቸው ላይ በመገኘት ለቀሪው የማህበረሰብ ክፍል በስነ ምግባር የታጀበ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል። የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚው የተለያዩ ባህሪያትን ሊያሳይ የሚችል ቢሆንም፤ የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚው ማህበረሰብ የአገልግሎቱ የገቢ ምንጭ በመሆናቸው እና ተገቢው እንክብካቤ ሊደረግላቸው ስለሚገባ ባስ ካፒቴኖች በትዕግስትና በትህትና ደንበኞችን የማስተናገድ ልምድ ሊያዳብሩ ይገባል። የደንበኞችን ምቾት ሊነሱ የሚችሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ተጠቃሚዎችን ከተግባራቸው እንዲታረሙ በማድረግ ካልሆነ ግን ለተቀረው ተገልጋይ ደህንነትና ምቾት ሲባል አገልግሎቱን እንዳያገኝ በማድረግ የደንበኞችን ምቾት በመጠበቅ ለአገልግሎቱ ቀጣይነት ያለው የገቢ ምጭ ማመንጨት ይቻላል በማለት አብራርተዋል።